የኢትዮጵያ ታሪክ

ኑብያ—አክሱም ዛጉዬ

አስክ ፡ ዐፄ ፡ ይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ።

ተጻፈ ፡

ከተክለ ፡ ጻድቅ ፡ መኩሪያ

LIBRARY

፭ኛ መጽሐፍ ።

ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በነገሡ ፡ በ፳፯ኛው ፡ ዓመት ፡ ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ በትንሣኤ ፡ ዘጉባኤ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ።

አዲስ ፡ አበባ ፡ ጥር ፡ ፲፮ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፺፭ ፡ ዓ. ም.



ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።



ግርማዊት እቴጌ መነን ።



ልዑል መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት አልጋ ወራሽ ።

መ ቅ ድ ም ።

የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ የነግነት ፡ ዘመን ፡ ረዥም ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ በዚህ ረዥም ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ በገሪቱ ፡ ላይ ፡ የውስጥ ፡ ጦርነትም ፡ የእስተዳደርና ፡ የዳኝነት የንግድና ፡ የሽቀጥ ፡ መለዋወጥ ፡ ከውጭ ፡ መንግሥታት ፡ ጋር ፡ የግንኙነት ፡ ጉዳይ ፡ መፈጸሙ ፡ ሳይቀር ፡ በድንጋይም ፡ በብራናም ፡ ላይ ፡ ሠፍሮ ፡ የምናገኘው ፡ እስካሁን የምናውቀው ፡ የታሪክ ፡ ጽሑፍ ፡ አነስተኛ ፡ ነው ። የየዘመኑን ፡ ታሪክ ፡ እግር ፡ በእግር ፡ እየተከተለ ፡ አዘጋጅቶ ፡ ያከታተለው ፡ ከለመኖሩ ፡ የተነሣ ፡ ሙሉ ፡ የኢትዮጵያን ታሪክ ፡ ለማግኘት ፡ ለማስረዳትና ፡ ለመረዳት ፡ ጸሐፊም ፡ አንባቢም ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ ችግረኛ ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ስለቀደሞው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ እዳር ፡ ቆመን ፡ መመልከት ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ጸሐፊ ፡ ያዘጋጀውን ፡ አነስተኛ ፡ ጽሑፍ ፡ ለይተን ፡ ማንበብና ፡ መተረክ ፡ ሳይሆን ፡ እውስጥ ፡ ገብተን ፡ የረዥሙን ፡ ዘመን ፡ ታሪክ ፡ በድንጋይና ፡ በብራና ፡ ከተጻፈው ፡ ላይ ፡ ለማዳረስ ፡ የፈለግን ፡ እንደሆነ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ተበታትኖም ፡ ተወሳስቦም ፡ እንደሚገኝ ፡ መረዳታችን ፡ አይቀርም ።

ካፄ ፡ ዐምደ ፡ ጽዮን ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ (ሸ፤፻፲፴፰-ሸ፫፻፶፰ ፡ ዓ፡ ም ፡) ወዲህ ፡ ሞላ ፡ ከጐደል ፡ የነገሥታቱ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ በግዕዝ ፡ ቋንቋ ፡ እተጻፈበት ፡ ውስጥ ፡ ያገሪቱ ፡ ታሪክ ፡ ባጫጭሩ ፡ እየተወሳ ፡ ከማለፍ ፡ በቀር ፡ እንደሌሎቹ ፡ መንግሥታት ታሪክ ፡ በአማርኛ ፡ እንኳ ፡ ቢቀር ፡ በዚያው ፡ በዘመኑ ፡ በሚጻፍበት ፡ በግዕዝ ፡ ቋንቋ ፡ አጥጋቢ ፡ ታሪክ ፡ አይገኝም ። ከነገሥታቱ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ውስጥ ፡ ያንዱ ንጉሥ ፡ የተገኘ ፡ እንደሆነ ፡ የሌላው ፡ ይጠፋል ፡ ወይም ፡ የተገኘው ፡ ላንድ ፡ ምዕራፍ ፡ የሚበቃ ፡ ሐተታ ፡ ለመስጠት ፡ የማያስችል ፡ ይሆናል ። የዚህም ፡ ሁሉ ምክንያት ፡ የፊተኛው ፡ በዮዲትና ፡ የኋለኛው ፡ በግራኝ ፡ መሐመድ ፡ መነሣት ፡ ቢመክኝ ፡ ከግራኝ ፡ ወዲህ ፡ ያለውም ፡ በጐንደር ፡ የነበሩት ፡ የነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መሉና ፡ ዝርዝር ፡ ታሪክ ፡ ይጐድለዋል ።

ከዚያ ፡ የበለጠ ፡ ደግሞ ፡ ያገሪቱና ፡ የመንግሥቱ ፡ ታሪክ ፡ የፖለቲካውና ፡ የኤኮኖሚው ፡ ሁኔታ ፡ የሚታወቀው ፡ በልክ ፡ ነው ። እንደዘመኑ ፡ ልማድ ፡ የዚህ ፡ ክፍል ፡ ሐላፊዎች ፡ በየዘመኑ ፡ ያሉት ፡ ጸሐፍተ ፡ ትእዛዛት ፡ ናቸው ። የነርሱም የጸሐፊነት ፡ አቅማቸው ፡ በዚሁ ፡ በጠባቡና ፡ የንጉሥን ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ በመጻፍ ፡ ብቻ ፡ የተወሰነ ፡ ይሁን ፤ ወይም ፡ ከዚህ ፡ አልፈው ፡ በሰፈው ፡ መጻፍ ፡ እያሰቡ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ የተቸገሩበት ፡ ዘረፉ ፡ የማንረዳው ፡ ምክንያት ፡ ይኑር ፡ አናውቅም ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ካፄ ፡ ዐምደ ፡ ጽዮን ፡ ወዲህ ፡ ያለው ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ሲገኝ ከዚያ ፡ በፊት ፡ ያለው ፡ የአክሱሞችና ፡ የዛጉዬዎች ፡ ታሪክ ፡ ከዚህ ፡ የባሰ ፡ ነው ። ታሪክ ፡ ነገሥት ፡ በሚባለው ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ከጻድቃንና ፡ ከሰማዕታት ፡ ገድልና ፡ ድርሳን ፡ ጋር ፡ ተሰባጥሮ ፡ የሚገኘው ፡ የነገሥታቱ ፡ ታሪክ ፡ እርስ ፡

በርሱ ፡ ከመለያየቱ ፡ በቀር ፡ ዛሬ ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ሐውልት ፡ ከሳባውና ፡ ከግሪኩ ፡ ከግዕዙም ፡ ላይ ፡ ወደአማርኛ ፡ የተተረጐመ ፡ እንደሆነ ፡ የዚህ ፡ ትርጉም ፡ እስካሁን ፡ ሲነበብና ፡ ሲታመንበት ፡ የኖረውን ፡ የዚያኛውን ፡ ጽሑፍ ፡ ሲሸረው ስሙንም ፡ በሌላ ፡ ዓይነት ፡ ሲጠራው ፡ እናገኛለን ። ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ ታሪክ ፡ ነገሥቱ ፡ አብርሃ ፡ ያለውን ፡ የሐውልቱ ፡ ጽሑፍ ፡ ሚዛና ፡ ሲለው ፤ ታሪክ ፡ ነገሥቱ ፡ አሪታዊ ፡ ያደረገውን ፡ ንጉሥ ፡ ሐውልቱ ፡ አረማዊ ፡ ሲያደርገው ፡ ይገኛል ። ነገር ፡ ግን ፡ እንደዚህ ፡ የተለያየበትን ፡ ምክንያት ፡ እዋናው ፡ መጽሐፉ ፡ ውስጥ፡ ስንገባ ፡ እናገኘዋለንና ፡ አሁን ፡ በዚህ ፡ በመቅድሙ ፡ ላይ ፡ መድገም ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም ።

በዚህ ፡ ዓይነት ፡ የሚገኘውን ፡ ያገራችንን ፡ ታሪክ ፡ እንደዚሁ ፡ እንዳለ ፡ ያንባቢን ፡ አሳብ ፡ እያባዘነ ፡ ኑሮውን ፡ እንዲቀጥል ፡ ልንተወው ፡ አይገባም ። ለዘመድ ፡ የሚችለውን ፡ ጠበኛ ፡ ታሪክ ፡ ማዘመድ ፤ የተዘባረቀውን ፡ መልክ ፡ ሰጥቶ ፡ ማከታተል ፤ ለታረቅ ፡ የማይችለውንም ፡ አስታራቂ ፡ ማስረጃ፡ እስኪገኝ ፡ ድረስ ፡ በግልጽ ፡ ለየብቻ ፡ አስቀምጠ ፡ ፍርዱን ፡ ለአንባቢ ፡ መተው ፡ የሚቻልበትን ፡ ዘዴ ፡ መፈለግ ፡ የንባብና ፡ የጽሕፈት ፡ የመተረክም ፡ ልማድ ፡ አለኝ ፡ ለሚለው ፡ ሁሉ ፡ ግዴታውም ፡ ባይሆን ፡ ተግባሩ ፡ ነው ። ያንዳንድ ፡ አገሮችም ፡ ታሪክ ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ሲኖር ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ ለተከልና ፡ ለደራጅ ፡ የቻለው ፡ በየዘመኑ ፡ በተነሡት ፡ ጸሐፊዎች ፡ ትጋት ፡ ነው ። በገራችንም ፡ በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ እነአቶ ፡ አጽሜ ፡ እነአለቃ ፡ ታዬ ፡ እነብላቴን ፡ ጌታ ፡ ሳሩይ ፡ የደከሙ ፡ መሆናቸውን ፡ ሰናስታውስ ፡ አስታውሰንም ፡ ሰናመሰግን ፡ ማለፍ ፡ አይገባንም ።

እላይ ፡ ከፍ ብሎ ፡ በአመለከትኋቸው ፡ ምክንያቶች ፡ እፕሮግራም ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ትምህርት ፡ ሊሰጥበት ፡ የሚችል ፡ በአማርኛም ፡ በግዕዝም ፡ የታተመ ፡ መጀዳውን ፡ የተጻፈ ፡ ደንበኛ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ከለመኖሩ ፡ የተነሣ ፡ ከውጪ ፡ አገር ፡ ተቀጥረው ፡ የመጡት ፡ መምህራን ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ መጽሐፍና ፡ በየግል ፡ ቋንቋቸው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ታሪክችንን ፡ ለወጣቶቻችን ፡ ማስተማራቸውን ፡ በትምህርት ፡ ሚኒስቴር ፡ ውስጥ ፡ በምሥራፅት ፡ ጊዜ ፡ ተረዳሁ ። ከሌላው ፡ ልንደርስበት ፡ ከልቻልነው ፡ ዕውቀትና ፡ ጥበብ ፡ አልፈው ፡ ፊደልም ፡ መረቀትም ፡ ብርዕም ፡ ዕውቀትም ፡ ሳናጣ ፡ የገዛ ፡ ታሪክችንን ፡ ፈረንጆች ፡ በመጽሐፋቸውና ፡ በቋንቋቸው ፡ ወጣቶቻችንን ፡ ማስተማራቸው ፡ ምን ፡ ያህል ፡ የውርደት ፡ ስሜት ፡ እንደሚሰጥ ፡ ላንባቢ ፡ መግለጽ ፡ የሚያስፈልግ ፡ አይመስለኝም ።

ይህ ፡ ሁኔታ ፡ ስለአሳዘነኝ ፡ በነሰው ፡ ዕውቀቴ ፤ በልጅነት ፡ አስተያየቴ ፤ መንግሥታችን ፡ በተመለሰበትና ፡ አገርን ፡ የማገልገል ፡ አምሮት ፡ በሚያጣድፍበት ፡ በሸ፱፻፴፪ ፡ ዓ፡ ም፡ ከደንበኛው ፡ ሥራዬ ፡ ውጭ ፡ የዚያን ፡ ጊዜው ፡ የመረዳት ፡ አቅሜ ፡ በፈቀደልኝ ፡ መጠን ፡ ካዜ ፡ ቴዎድሮስ ፡ እስከ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የሚባለውን ፡ ጽሬ ፡ አሳተምሁ ። ይኸውም ፡ መጽሐፍ ፡ እንደ ፡ ሠጸሕፍት ፡ ሁሉ ፡ ከንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ የነቀፋ ፡ ጠጠር ፡ ቢወረ

ወርበትም ፡ በጠቅላላው ፡ ሕዝብንም ፡ ትምህርት ፡ ቤቶችንም ፡ መጥቀሙ ፡ አይከ
ድም ። የዚሁም ፡ ማስረጃ ከርሱ ፡ የተሻለ ፡ እስኪገኝ ፡ ድረስ ፡ ከትምህርት ፡
መስጫ ፡ ፕሮግራም ፡ ውስጥ ፡ ተመድቦ ፡ ፮ ፡ ጊዜ ፡ እየተደጋገመ ፡ መታተሙ ፡ ነው፡

ይኸን ፡ የመዠመሪያውን ፡ መጻሬ ፡ ሁለተኛውን ፡ ለመጻፍ ፡ ስለገፋፋኝ ፡
ከትምህርት ፡ ሚኒስቴር ፡ እንዳለሁ ፡ ያጋመስሁትን ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ባቡር ፡ መቆ
ጣጠሪያ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ከተዛወርሁ ፡ ወዲህ ፡ ከአፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ዠምሮ
እስከ ፡ አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ዘመን ፡ ያለውን ፡ ታሪክ ፡ አዘጋጅቼ ፡ ለማሳተም ፡ ቻልሁ ።
በዚሁ ፡ መጽሐፍ ፡ በመቅድሙ ፡ ላይ ፡ በገጽ ፡ ፲፭ ፡ እንዳመለከትሁት ፡ ከፄ ፡
ልብነ ፡ ድንግል ፡ ወዲህ ፡ ያለውን ፡ ጽሬ ፡ ከሳተምሁ ፡ በኋላ ፡ በአሳቤ ፡ የተተከው
ከሥር ፡ መንግሥታችን ፡ ከተመሠረተበት ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ አፄ ፡ ልብነ ፡
ድንግል ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ ለማጥናትና ፡ ለመጻፍ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ለዚሁ ፡
የሚጠቅሙኝን ፡ ከአንዳንድ ፡ መጻሕፍት ፡ ላይ ፡ እየለቀምሁ ፡ ጽሑፉን ፡ መጻፍ ፡
ዠምሬ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ገጽ ፡ ግድም ፡ የሚሆን ፡ የእጅ ፡ ጽሑፍ ፡ እንዳዘጋጀሁ ፡ ወደ
ፓሪስ ፡ ለሥራ ፡ ታዝዠር ፡ ሄድሁ ። በፓሪስ ፡ አምበሳድ ፡ የተመደበልኝን ፡ የጸሐ
ፊነት ፡ ሥራ ፡ እየሠራሁ ፡ የታሪኩንም ፡ ዝግጅት ፡ በድርብ ፡ ለመቀጠል ፡ ሞክሬ ፡
ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ የመቀጠል ፡ አምሮት ፡ ቢኖረኝ ፡ በአምባሳድ ፡ ከለው ፡
ከተርታ ፡ የጸሐፊነት ፡ ሥራ ፡ ጋር ፡ ለመቀጠል ፡ ጣዕም ፡ ስላጣሁበት ፡ የታሪኩን ፡ ሥራ ፡
ወደፍጻሜ ፡ ለማድረስ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ነፃ ፡ ጊዜ ፡ እንዲፈቀድልኝ ፡ ለግርማዊ ፡
ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በደብዳቤ ፡ አመለከትሁ ። ግርማዊነታቸውም ፡ በተለመደ ፡ የጽሑፍ ፡
ደጋፊነታቸው ፡ የጠየቅሁትን ፡ ጊዜ ፡ ፈቀዱልኝ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቀድሞውኑ ፡ ከማውቀውና ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ይዣቸው ፡ ከሄድ
ሁት ፡ ጽሑፎች ፡ በቀር ፡ ፩ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ፓሪስ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ እየተመላለስሁ ፡
የታሪካችንን ፡ ጽሑፍና ፡ ማስረጃ ፡ የተገኘውን ፡ ያህል ፡ እየሰበሰብሁ ፡ ይኸን ፡ ከሥር ፡ ከኑብያ ፡
መንግሥት ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ አፄ ፡ ይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ ጽሑፍ ፡ ለማዘጋ
ጀት ፡ በቃሁ ። በዚሁም ፡ የፈረንሳዊን ፡ መንግሥት ፡ የቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ባለ
ሥልጣኖችና ፡ አገልጋዮች ፡ ስለአቀባበላቸውና ፡ ስለአደረጉልኝ ፡ የዘወትር ፡ አገ
ልግሎት ፡ ምሥጋናዬ ፡ ይድረሳቸው ።

ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ በመዠመሪያው ፡ ክፍል ፡ የኑብያ ፡ (ናፓታና ፡ መርዌ) ፤
በሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ የአክሱም ፤ በሦስተኛው ፡ ክፍል ፡ የዛጉዬ ፡ ሆኖ ከሦ
ስት ፡ ላይ ፡ ተከፍሎ ፡ እስከ ፡ አፄ ፡ ይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ድረስ ፡ (ሺ፪፻፷ ዓ፡ም)
ያለው ፡ ጥንታዊ ፡ ታሪካችን ፡ በኔ ፡ አስተያየትና ፡ አገላለጥ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ይገኝ
በታል ። አሁን ፡ የያዝነው ፡ ሥልጣኔና ፡ ቋንቋ ፡ ምንጩ ፡ ከኑብያ ፡ ይልቅ ፡ አክሱም ፡
መሆኑን ፤ በኑብያና ፡ በአክሱም ፡ መንግሥት ፡ መከከል ፡ ያለውንም ፡ ልዩነት ፡
በጽሑፉ ፡ ውስጥ ፡ እንረዳለን ።

መቅድም ፡ የኢትዮጵያን ፡ ታሪክ ፡ ለመጻፍ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ታሪክ ፡ ማወቅ፡ ብቻውን ፡ አይበቃም ። የቀድሞ ፡ ጸሐፍት ፡ ትእዛዛት ፡ ከድክማቸው አንዱ ፡ ይህ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። ነገር ግን የኑብያን ፡ ለማወቅ ፡ የግብፅን ፡ ታሪክ ፡ ማወቅ፡ አስፈላጊ ፡ ሲሆን ፡ የአክሱምን ፡ ታሪክ ፡ ለመረዳት የግሪክንና ፡ የሮማን ፡ የቀሩ ስጥንጥንያን ፡ (ታናሽ ፡ ሮም) ፡ እንደዚሁም ፡ የደቡብ ፡ ዓረብን ፡ አገሮች ፡ ታሪክ ፡ በዝርዝርም ፡ በደንብ ፡ በመጠኑ ፡ ማወቅ ፡ ያሻል ። ብዚህ ፡ ምክንያት ፡ ታሪኩ፡ አስገድዶ ፡ እንጂ ፡ ገዱን ፡ ለማብዛት ፡ ሳይሆን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የጠቀስኋቸውን ፡ አገሮች ፡ እንደዘመኑና ፡ እንደክፍሉ ፡ ካገራችን ፡ ታሪክ ፡ ጋር ፡ ያወራረስሁት ፡ እዚያው ፡ እየታሪኩ ፡ ላይ ፡ የሚገኘው ፡ የአንባቢንና ፡ የተማሪን፡ አእምሮ ፡ እንዲያገለግል ፡ አመኛለሁ ። ይኸን ፡ መጽሐፍ ፡ ለማዘጋጀት ፡ ያገለገሉኝን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መጻሕፍት ፡ እዚያው ፡ እዋናው ፡ መጽሐፍ ፡ አካል ፡ ውስጥ ፡ በየምዕራፉ ፡ ስለጠቀስኋቸው ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ መዘርዘር ፡ አስፈላጊ ፡ አልመሰለኝም ።

ይኸን ፡ መጽሐፍ ፡ (ሌሎችንም) ለማዘጋጀት ፡ የተጠቀምሁባቸው ፡ ቋንቋዎች ፡ ግዕዝ ፡ ፈረንሳዊኛና ፡ ኢጣልያንኛ ፡ ሲሆኑ ፡ በነዚህ ፡ ቋንቋዎች ፡ የተጻፉትን ፡ መጻሕፍት ፡ በየመሥመሩ ፡ እየተከታተልሁ ፡ በመሰብሰብ ፡ በማነፃፀር፡ ከጻፍሁ ፡ በኋላ ፡ በራሴ ፡ አስተያየት ፡ ለማብራራት ፡ ሞክሬያለሁ ። ፩ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በመድከምና ፡ በመሰልቸት ፡ ጊዜም ፡ በማጠር ፡ ለየጉዳዩ ፡ በቂ ፡ ሐተታ፡ ሰጥቼ ፡ የማስበውን ፡ ያህል ፡ የንባብ ፡ ወዝ ፡ ሳልሰጥ ፡ ማለፌ ፡ ትዝ ፡ የሚለኝን ፡ ለመደበቅ ፡ አልሻም ። ነገር ፡ ግን ፡ እንደዚህ ፡ ሆኖ ፡ ተከታትሎ ፡ ለወደፊት ፡ ጸሐፊ ፡ እንደሚመች ፡ ተዘጋጅቶ ፡ መቀመጡ ፡ ደግሞ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ዋጋ ፡ እንዳለው ፡ ስለማውቅ ፡ ከድካም ፡ የመነጨውን ፡ ደስታዬን ፡ ሊቀንስብኝ ፡ አይችልም ። ከኔ ፡ በፊት ፡ እንደዚህ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ባገኘው ፡ ኖሮ ፡ ለፍለጋ ፡ ለማገናዘብ ፡ ያጠፋሁትን ፡ ረዥም ፡ ጊዜ ፡ ይበልጥ ፡ ለማብራራትና ፡ በጥሩ ፡ ዘመናዊ ፡ ያነጋገር ፡ ቅርጽ ፡ ለማቃናት ፡ ስሠዋው ፡ ዛሬ ፡ ከዚህ ፡ የተሻለ ፡ ጽሑፍ ፡ ለማቅረብ ፡ በተቻለኝ ፡ ነበር ።

ከፓሪስ ፡ ከተመለስሁ ፡ በኋላም ፡ ይኸንኑ ፡ የእጅ ፡ ጽሑፌን ፡ ለማረም፡ ለማቃናት ፡ በማፍረስና ፡ በመጠገን ፡ አሳቤ ፡ ያረፈበት ፡ ጊዜ ፡ በልክ ፡ ነው ። እንደ ፡ ሌላው ፡ ሁሉ ፡ የዚህን ፡ ዓይነት ፡ ሥራ ፡ ለማከናወን ፡ የመንፈስን ፡ ጸጥታና ፡ ሰላም ፡ ከትዕግሥት ፡ ጋር ፡ ያስፈልጋል ። እነዚህም ፡ የአእምሮ ፡ መሰብሰብን ፡ ያስገኛሉ ። ሥራንም ፡ የሚያራምደው ፡ የአእምሮ ፡ መሰብሰብ ፡ ነው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ደስታና ፡ ጨዋታ ፡ ሌላም ፡ የኑሮ ፡ ዘርፍ ፡ የሚያበክኑ ፡ መሆናቸውን ፡ መደገም ፡ እናድርግና ፡ በበለጠ ፡ በሕይወት ፡ የሚደርስ ፡ ማናቸውም ፡ አሳዛኝ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ የነዚህ ፡ ሁሉ ፡ የሥራዎች ፡ ጠላት ፡ ሆኖ ፡ አእምሮንና ፡ መንፈስን ፡ እየበተነ ፡ ለነፋስ ፡ ሲሰጠው ፡ ነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ከውጥንና ፡ ከድቅን ፡

ሳያልፍ ፡ ይቀራል ። የዘመን ፡ ርዝማኔም ፡ ውጥኑን ፡ ፩ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ፈጽሞ ፡ ወደ መጥፋት ፡ ያደርሰዋል ። በዚህ ፡ ጠላት ፡ እጅ ፡ ላለመውደቅ ፡ ይኸውም ፡ ማለት ፡ የተሰበሰበ ፡ አእምሮ ፤ የረጋ ፡ መንፈስ ፡ ለማግኘት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ እርዳታ ፡ በመጠየቅ ፡ መጣጣር ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

እንግዴህ ፡ ከዚ ፡ ቱዎድሮስ ወደኋላ ፡ ወዳዜ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ተመልሼ ፡ ከኑብያ ፡ በአክሱምና ፡ በዛጉዬ ፡ በሸል ፡ እስከ ፡ አዜ ፡ ይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ደርሼ ፡ በመሉ ፡ ያገራችንን ፡ ታሪክ ፡ ለማዳረስ ፡ የሚቀረኝ ፡ ከዜ ፡ ይኩኖ ፡ አምላክ ፡ እስከ ፡ አዜ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ (፲፫-፲፮ኛ መቶ ፡ ዓ ፡ ምሕ) ያለው ፡ የሁለት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ጊዜና ፡ ታሪክ ፡ ነው ። ይኸንንም ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ለማውጣት ፡ ምኞቴ ፡ ነው ።

ማናቸውም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሥራና ፡ ፍጥረት ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ አስፈላጊው ፡ ነው ። ከዚያም ፡ በታች ፡ አንዱ ፡ ሰው ፡ የሚሠራው ፡ ለሌላው ፡ ሰው ፡ እንደመብልና ፡ እንደመጠጥ ፡ ግዴታ ፡ አስፈላጊውም ፡ ባይሆን ፡ ጠቃሚው ፡ ነው ። መጽሐፍም ፡ በማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ውስጥ ፡ የያዘው ፡ የጠቃሚነት ፡ ደረጃ ፡ ከቀድሞ ፡ ዝምሮ ፡ የነበረው ፡ ዛሬ ፡ ከፍ ፡ እያለ ፡ ሄዷል ።

ተማሪ ፡ ይማርበታል ፤ መምህር ፡ ያስተምርበታል ።

ወታደር ፤ ገበሬ ፤ ነጋዴ ፤ የእጅ ፤ ሞያተኛ ፡ ሁሉ ፡ ያላስተማሪ ፡ አእምሮውን ፡ ያስፋፋበታል ።

የታመመ ፤ ያዘነ ፤ የታሠረ ፤ እቤት ፡ የዋለ ፡ ሽማግሌ ፡ እግረ ፡ መንገዱን ፡ እየተማረ ፡ በመጽናናት ፡ መጥፎውን ፡ የችግር ፡ ዘመንና ፡ የሥራ ፡ መፍታት ፡ ጊዜ ፡ ያሳልፍበታል ።

ስለዚህ ፡ በምንችለውና ፡ ስጠታችን ፡ በሆነው ፡ መንገድ ፡ የጽሑፍ ፡ ምርት ፡ ለወገናችን ፡ እያበረከትን ፡ በዚሁም ፡ ወደኋላ ፡ የቀረውን ፡ ያገራችንን ፡ የሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ጉድለት ፡ በየቅርንጫፉ ፡ እንድናሻላው ፡ በቅንነት ፡ እመኛለሁ ።

ጥር ፲፭ ፡ ቀን ፲፱፻፺፩ ፡ ዓ ፡ ም ።

ተክለ ፡ ጻድቅ ፡ መኩሪያ ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

የኢትዮጵያ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የነገድ ፡ ስም ።

ዛሬ ፡ ባንድ ፡ በኢትዮጵያና ፡ በኢትዮጵያዊ ፡ ስም ፡ የረጋው ፡ ያገራችንና ፡ የሕዝቡ ፡ ስም ፡ ቀድሞ ፡ ብዙ ፡ ነበር ። በአሪት ፡ ዘፍጥረት ፡ ምዕራፍ ፡ ፱ ፡ ቍጥር ፡ ፲፫ ፡ በዚሁ ፡ መጽሐፍ ፡ ምዕራፍ ፡ ፲ ፡ ከቍጥር ፡ ፩ ፡ እስከ ፡ ፴፪ ፡ ያለው ፡ ጽሑፍ ፡ የኖህ ፡ ልጆች ፡ ሴም ፡ ካም ፤ ያፌት ፤ መሆናቸውን ፡ የካም ፡ ልጆች ፡ ኩሽ ፡ (ኩስ ፡ ቁስ) ፡ ሚስራይ ፡ ፋጥ ፡ ከነዓን ፡ መሆናቸውን ፡ እንደሚገልጸው ፡ የኩሽም ፡ ዘር ፡ በእስያ ፡ ደቡብ ፡ ከዚያም ፡ ወደ ፡ አፍሪካ ፡ ተሻግረው ፡ ተራብተው ፡ በር ክተው ፡ ከዛሬው ፡ ሱዳን ፡ ገምሮ ፡ እስከ ፡ ኤርትራ ፡ ባሕር ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ አገር ፡ ይዘው ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ በ፫ሺና ፡ በ፩ሺ ፡ ዓመት ፡ መከከል ፡ ሁሉ ፡ ግብፆች ፡ በሐውልታቸውና ፡ በብራና ፡ (ፓፒሩስ) ፡ ጽሑፋቸው ፡ (ሂዬሮግሊፍ) ፡ ላይ ፡ እንደተውት ፡ በሰፈው ፡ ኢትዮጵያን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የኩሽ ፡ አገር ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ የደቡብ ፡ ምድር ፡ ወይም ፡ የነሐስ ፡ የነሕሴ ፡ አገር ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ የፑንት ፡ አገር ፡ እያሉ ፡ ይጠሩት ፡ ነበር ። በዝርዝሩ ፡ እንደምናገኘው ፡ ነሕሴ ፡ ከነገደ ፡ ካም ፡ ይኖው ፡ ንጉሥ ፡ ተብሎ ፡ የተመደበ ፡ ስለሆነ ፡ ጅማ ፡ ያባ ፡ ጅፋር ፡ አገር ፡ ሸዋ ፡ የአምኃየስ ፡ አገር ፡ እንደሚባለው ፡ ሁሉ ፡ በመሪው ፡ ስም ፡ የነሕሴ ፡ አገር ፡ ማለታቸው ፡ ይሆናል ። ግማሾቹ ፡ ነሕሴ ፡ ማለት ፡ ጥቁር ፡ ማለት ፡ ስለሆነ ፡ የጥቁር ፡ አገር ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ይላሉ ። ደግሞ ፡ ከወባይ ፡ እስከ ፡ ኤርትራ ፡ ባሕር ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ አገር ፡ ግብፆች ፡ ፑንት ፡ ብለውት ፡ ይገኛሉ ። ለአማልክቶቻቸውና ፡ ለቤተ ፡ መቅደሳቸው ፡ የሚሆን ፡ ዕጣን ፡ ከርቤ ፡ ብርጉድ ፡ ለመውሰድ ፡ ወደፑንት ፡ ዘመትን ፡ ሲሉ ፡ አምላካቸው ፡ አሞን ፡ ፑንትን ፡ ሰጥቸ ፡ ሸለሁና ፡ ውጋና ፡ ውሰድ ፡ እንዳላቸው ፡ በጽሑፍ ፡ ይገኛል ።

ጌታችን ፡ በማቴዎስ ፡ ወንጌል ፡ ምዕራፍ ፡ ፲፪ ፡ ላይ ፡ እንደሚገኘው ፡ ንግሥተ ፡ አዜብ ፡ ይሽን ፡ ሕዝብ ፡ ለመፋረድ ፡ ትነሣለች ፡ .... ያለውን ፡ በኛ ፡ በግዕዝ ፡ አዜብ ፡ ማለት ፡ በደቡብና ፡ በምዕራብ ፡ መከከል ፡ ያለ ፡ አገር ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ በፈረንጅ ፡ ሁሉ ፡ የወንጌል ፡ ትርጓሜ ፡ ንግሥተ ፡ አዜብ ፡ የምንለ

ውን ፡ የደቡብ ፡ ንግሥት ፡ ስለሚል ፡ ነሕሴንና ፡ ጉንትን ፡ መደጐን ፡ እናድርግና ፡ ለዚሁ ፡ ጥንት ፡ ግብያች ፡ በጉርብትናም ፡ በግዛትም ፡ በነበሩበት ፡ ጊዜ ፡ የደቡብ ፡ አገር ፡ ከሚሉት ፡ ጋር ፡ ይገናኛል ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ግብያች ፡ የኩሽ ፡ ሕዝብ ፡ የሠፈረበትን ፡ አገር ፡ የደቡብ ፡ ወይም ፡ የኩሽ ፡ አገር ፡ ሲሉ ፡ ንግሥት ፡ አዜብ ፡ በኋላ ፡ ከመጡት ፡ ከነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ውስጥ ፡ ስለሆነች ፡ በመሬትና ፡ ባገሩ ፡ ከኩሽ ፡ ሕዝብ ፡ ትገናኛለች ፡ እንጂ ፡ የርሷ ፡ ዘር ፡ የመጣበት ፡ የሳባና ፡ የዮቅጣን ፡ ዘር ፡ ከካምና ፡ ከኩሽ ፡ ዘር ፡ ልዩነት ፡ እንደአለው ፡ አንዘነጋም ።

የቀረው ፡ ደግሞ ፡ እንደዛሬው ፡ አጠራራችን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሲል ፡ ይገኛል ። ለምሳሌ ፡ ከግሪኮቹ ፡ ውስጥ ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ በ፬ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ላይ ፡ የነበረው ፡ የአዲሴውስና ፡ የኤሊያስ ፡ ጸሐፊ ፡ ሖሜር ፡ በተለይ ፡ በኤሊያስ ፡ (ድ) ፡ መጽሐፍ ፡ ላይ ፡ ምዕራፍ ፡ ፭ና ፡ በሌላውም ፡ ክፍል ፤ የታሪክ ፡ አባት ፡ የሚባለው ፡ በ፭ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ላይ ፡ የነበረው ፡ ሄሮዱት ፡ በታሪክ ፡ መጽሐፉ ፡ በ፱ኛውና ፡ በ፫ኛው ፡ በ፩ኛውና ፡ በ፯ኛው ፡ ክፍል ፡ ኢትዮጵያ ፡ ይላሉ ። ከእስራኤሎችም ፡ ወገን ፡ ይሽሙ ፡ ነው ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ በ፩ሺ፩መቶ ፡ ዓመት ፡ ላይ ፡ የነበረው ፡ ዳዊት ፡ በመዝሙሩ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሲል ፡ በ፯ ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ የነበረው ፡ ኢሳይያስ ፡ ደግሞ ፡ በትንቢቱ ፡ ምዕራፍ ፲፩ ፡ ቁጥር ፲፩ ፡ ምዕራፍ ፲፰ ፡ ቁጥር ፩-፪ ፤ ሶፎንያም ፡ በምዕራፍ ፫ ፡ ቁጥር ፲ ፡ የኩሽ ፡ አገር ፡ ሲሉ ፡ ይገኛሉ ። ጓደኞቹው ፡ ዕንባቆም ፡ ደግሞ ፡ በምዕራፍ ፫ ፡ ቁጥር ፯ ፡ መልሰ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ይላል ። እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ የጥንት ፡ ጸሐፊዎችና ፡ ነቢያት ፡ ስለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ተግሣፅና ፡ ምክር ፡ ወይም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የጸሎትና ፡ የምስጋና ፡ ቃል ፡ ሲያቀርቡ ፡ እግረ ፡ መንገዳቸውን ፡ ያገራችን ፡ ጉዳይ ፡ ሲያጋጥማቸው ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ የኩሽ ፡ አገር ፡ ሲሉን ፡ ቆዩ ። በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ ደግሞ ፡ የሴም ፡ ዘሮች ፡ ነገደ ፡ ሳባና ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ከደቡብ ፡ ዓረብ ፡ የኤርትራን ፡ ባሕር ፡ እየተሻገሩ ፡ ከካምና ፡ ከኩሽ ፡ ዘር ፡ ጋር ፡ ተደባልቀው ፡ ወይም ፡ በጦር ፡ አሸንፈው ፡ አብረው ፡ በተቀመጡ ፡ ጊዜ ፡ በስም ፡ ላይ ፡ ስም ፡ እየበረከተ ፡ ሄደ ። የቀድሞዎቹ ፡ በኑብያ ፡ መንግሥታቸውን ፡ አስፍተው ፡ ኢትዮጵያ ፡ የኩሽ ፡ አገር ፡ እየተባሉ ፡ ሲቀመጡ ፡ በሥልጣኔ ፡ በጽሑፍ ፡

በቋንቋ ፡ የግብፅን ፡ ሲከተሉ ፡ በኋላ ፡ የመጡት ፡ ደግሞ ፡ በትግሬና ፡ በሐማሴን ፡ እንደዚሁም ፡ በዙሪያው ፡ ከተማቸውን ፡ እየከተሙ ፡ ከደቡብ ፡ ዓረብ ፡ ይዘውት ፡ የመጡትን ፡ ከአሶር ፡ ከከለዳውያን ፡ ከሬንቄ ፡ የመነጨውን ፡ የሳባ ፡ ቋንቋና ፡ ሬደል ፡ ለዛሬ ፡ ሬደላችን ፡ ቋንቋና ፡ አባት ፡ የሆነውን ፡ ከሥልጣኔያቸውና ፡ ከል ማዳቸው ፡ ጋር ፡ ይዘው ፡ ተቀመጡ ።

ይሽን ፡ የልዩነት ፡ ሁኔታ ፡ የዛሬ ፡ ሊቃውንት ዮሴፍ ፡ ሀለቪ ፡ (JOSEPH HA LEVI)፡ ኤድዋርድ፡ግላዘር፡ (EDUARD GLASER)፤ኮንቲ፡ሮሲኒ(CONTI ROSSINI)፤ ዢ ፡ሪክማን፡(G. RYCKMANS) ሌሎችም ፡ በዚህ፡ገጽ ፡ ስማቸውን ፡ ዘርዝሬ ፡ የማል ጨርሰው ፡ ለማጣራት ፡ እንደ፡ ደከሙ፡ ወደፊትም ፡ ያሉት ፡ ጨርሰው ፡ ማጣራት፡ እስኪ ችሉ ፡ ድረስ ፡ የዛሬ፡ ዘመን፡ ጸሐፊዎች፡ በብዙ፡ ምርመራ ፡ እያጣሩና ፡ እየለዩ ፡ እጻፉ በት ፡ እዛሬው ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ የጥንት ፡ ጸሐፊዎች ፤ ነቢያት ፤ ነገሥታት ፤ ነገሩን ፡ እቅርብ ፡ ሰይክታተሉ ፡ በሩቅ ፡ ሆነው ፡ ሲናገሩም ፡ ሲጽፉም ፡ አንድ ፤ ጊዜ ፡ ኢት ዮጵያ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ኩሽ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ነገደ ፡ ካም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ነገደ ፡ ሴም ፡ እያሉ ፡ ይጠሩት ፡ ነበር ። እንደዚሁም ፡ ነገደ ፡ ኩሽን ፡ ከነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ የደቡብ ፡ ዓረብን ፡ ነገደ ፡ ሳባ ፡ ከኖብያው ፡ ሳባ/ ፡ ሰባ–ሻባ/ ፡ ጋር ፡ እያደበለቁ ፡ ይጽፉ ፡ ያኖው ፡ የሠራውን ፡ ለዚህኖው ፡ ይሽኖው ፡ የሠራውን ፡ ለዚያኖው ፡ እየሰጡ ፡ ሲጽፉም ፡ ይገኖሉ ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ መልሰው ፡ የሚለዩበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ።

ለምሳሌ ፡ ዳዊት ፡ በፅፏኖው ፡ መዝሙሩ ፡ በአማርኖው ፡ ላይ ፡ የተርሴስና ፡ የደሴቶች ፡ ነገሥታት ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ያገባሉ ፡ ከለው ፡ ቀጥሎ ፡ የሻባና ፡ የሳባም ፡ ነገሥታት ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ ያቀርባሉ ፡ ብሎ ፡ ለይቷል ። በግዕዝ ፡ ቋንቋ ፡ ዓረብኛ ፡ ሬደል ፡ስለሌለ፡ ሻባ ፡ ያለውን ፡ ሳባ ፤ ሳባ ፡ ያለውን ፡ ደግሞ ፡ በዓረብ ፡ አገር ፡ ያለ መሆኑን ፡ ለመግለጽ ፤ ነገሥት ፡ ሳባ ፡ ወዓረብ ፡ ጋዳ ፡ ያመጽኡ ፡ ብሎታል ። ይህም ፡ አጭር ፡ የዳዊት ፡ ቃል ፡ የዛሬ ፡ መርማሪ ፡ ሊቃውንት ፡ በሰፊው ፡ ከመረመሩት ፡ ጋር ፡ ተገናኝቷል ። በኖብያ ፡ ውስጥ ፡ ከኩሽ ፡ የተወለዱት ፡ ልጆች ፡ ሻባ ፡ ይባሉ ፡ እንደነበረ ፡ በርሱም ፡ ነገደ ፡ ሻባ ፡ የሚባል ፡ ዘር ፡ እንደነበረ ፡ ለመረዳት ፡ ሳባ ፡ ኖባ ፡ ከሚባለው ፡ ካገራችን ፡ ጽሑፍም ፡ ከዳዊት ፡ መዝሙርም ፡ በቀር ፡ በኖብያ ፡ በኋ ኖው ፡ መዶ ፡ ዓመት ፡ ላይ ፡ ስሙና ፡ ሥራው ፡ በግብፃውያኑ ፡ ሐውልትና ፡ ብራና ፡

በትክክል ፡ ተጽፎ ፡ የሚገኘው ፡ ግብፅን ፡ የገዛው ፡ ንጉሥ ፡ ሽባክ ፡ የሚባለው ፡ ስሙ ፡ ይገልጻል ።

በሽባ ፡ ላይ ፡ ካ ፡ የተጨመረበትን ፡ ምክንያት ፡ ሙሴ ፡ ብሩግሽ ፡(BRUGSCH) የሚባሉት ፡ የጀርመን ፡ ሊቅ ፡ አኤቲዎፒካ ፡ በሚባለው ፡ መጽሐፋቸው ፡ ካ ፡ በጥንታዊያን ፡ የግብፆች ፡ የሰዋስው ፡ ሥርዓት ፡ ዘርፍ ፡ አያያዥ ፡ መሆኑን ፡ ገልጸዋል ። ይኸውም ፡ ሽባ ፡ ካ ፡ ማለት ፡ የሽባ ፡ ማለት ፡ ነው ። የርሱም ፡ ተከታይ ፡ ልጁ ፡ መጠሪያ ፡ ስሙ ፡ ከባቱ ፡ ሳይርቅ ፡ ሽባቶ ፡ ካ ፡ ይባል ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ እላይ ፡ እንደአልነው ፡ በኖብያ ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ መንግሥት ፡ ሽባ ፡ (ሳባ) ፡ የሚባል ፡ ሲኖር ፡ ከነገደ ፡ የ-ቅጣንም ፡ ወገን ፡ በደቡብ ፡ ዓረብ ፡ የነበረው ፡ ወደ ፡ ዛሬዪቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሰሜንም ፡ የዘለቀው ፡ ንግሥተ ፡ ሳባም ፡ የተጠራችበት ፡ የሳባ ፡ ዘር ፡ ለየብቻ ፡ መኖሩን ፡ ይኸም ፡ ሁለቱ ፡ እየተደባለቀ ፡ የጥንትን ፡ ጸሐፊዎች ፡ ያስቸገራቸው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ከተመለከትን ፡ በኋላ ፡ ወደዋናው ፡ ጉዳይ ፡ እንመለስ ።

እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ የጥንት ፡ ጸሐፊዎች ፡ ግብፆችም ፡ እስራኤሎችም ፡ ግሪክችም ፡ ግማሾቹ ፡ የኩሽ ፡ አገር ፡ የቀሩት ፡ ኢትዮጵያ ፡ እያሉ ፡ ሲጠሩን ፡ አሁን ፡ ባለንበት ፡ የፖለቲካና ፡ ያገር ፡ ክፍል ፡ የምንገኘውን ፡ ኢትዮጵያውያኖችን ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ከዛሬው ፡ ቱኒዚና ፡ ማሮክ ፡ ከሊቢያና ፡ ግብፅ ፡ ከፍልስጥኤም ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ በኤርትራ ፡ ባሕር ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ እስከ ፡ ሕንድ ፡ ውቅያኖስ ፡ ጠረፍ ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ የዛሬውን ፡ የዓረብንም ፡ የሱዳንንም ፡ በመከከል ፡ የሚገኘውን ፡ ያሁኑን ፡ የኛንም ፡ አገር ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ እየለዩ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እየ ደባለቁ ፡ ነው ።

ይኸም ፡ እንደሙሉ ፡ ስሕተት ፡ እንዳይቆጠር ፡ በዙሪያችን ፡ ከሚገኙት ፡ ከነዚህ ፡ ሕዝቦች ፡ ጋር ፡ ዘራችን ፡ ልማዳችን ፡ ቋንቋችን ፡ ከሥር ፡ ከመሠረቱ ፡ እየተገናኘ ፡ ተደባልቆ ፡ በመኖሩ ፡ ነው ። ደግሞ ፡ ረኃብ ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ እንደኛው ፡ ነገድ ፡ ተሰዶ ፡ ወደ ፡ እንደኛው ፡ ነገድ ፡ አገር ፡ ሄዶ ፡ ይደባለቃል ። ከመከከላቸው ፡ አንድ ፡ ኃይለኛ ፡ የነገድ ፡ አለቃ ፡ ተነሥቶ ፡ ማስገበር ፡ ሲፈልግ ፡ የሌላውን ፡ አገር ምርኮ ፡ ወደራሱ ፡ አገር ፡ የራሱን ፡ አገር ፡ ሕዝብ ፡ በወራሪነት ፡ በሌላው ፡ አገር ፡ ሲተወው ፡ ይህን ፡ በመሰለው ፡ ሁኔታ ፡ ሕዝብ ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ ሲዘዋወርና ፡ ሲደባለቅ ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ዘሩ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ጽሕፈቱና ፡ ቋንቋው ፡ መጠሪያ ፡

ስሙም ፡ ልማዱና ፡ ጥበቡም ፡ እየተደበላለቀና ፡ እየተደቀለ ፡ ለመለየት ፡ ያስቸግራል ። ስለዚህ ፡ ይህን ፡ ችግር ፡ ማለፍና ፡ መለየት ፡ የማይቻል ፡ በሩቅ ፡ ያለ ፡ የጥንት ፡ ጸሐፊ ፡ በደፈና ፡ የኩሽ ፡ አገር ፡ ወይም ፡ ኢትዮጵያ ፡ ብሎት ፡ ያልፋል ።

የዛሬ ፡ ጸሐፊና ፡ መርማሪም ፡ ነገሩን ፡ ላበጥር ፡ ብሎ ፡ ሲነሣ ፡ የዘመኑ ፡ ርቀት ፤ በዘመኑ ፡ የተደራጀው ፡ ጽሑፍ ፡ በማነሱ ፤ የፊደሉና ፡ የቋንቋው ፡ የባሕሉና ፡ የልማዱ ፡ ድብልቅነት ፡ እየተደቀነበት ፡ ችግሩን ፡ በሙሉ ፡ ማለፍ ፡ እያቃተው ፡ በጥንታዊው ፡ በኢትዮጵያና ፡ በሌላውም ፡ አገር ፡ የቀድሞ ፡ ታሪክ ፡ ቢሆን ፡ በዛሬው ፡ ጊዜ ፡ በጽሑፍ ፡ ለሕዝብ ፡ የሚያቀርበው ፡ የሥራ ፡ ፍሬ ፡ ሞላ ፡ ከጐደል ፡ ከመሆን ፡ አይዘልም ።

እኛ ፡ የጉዳዩ ፡ ባለቤቶች ፡ ለሥራው ፡ ችላ ፡ ባልንበት ፡ ዘመን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ታሪክ ፡ የጻፉት ፡ ጀምስ ፡ ብሩስ ፤ ሞሪዮ ፤ ኩልቦ ፤ ከንቲ ፡ ሮሲኒ ፤ ካሜረር ፤ ባጅ ፤ እንደዚሁም ፡ ሌሎቹ ፡ ሁሉ ፡ የጥንቱን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ታሪክ ፡ ለማግኘት ፡ ከኛ ፡ ታሪክ ፡ ነገሥትና ፡ ክብረ ፡ ነገሥት ፡ ተፈላልገው ፡ የሚበቃቸውን ፡ ያህል ፡ ሲያጡ ፡ ስለኛ ፡ አገር ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊትና ፡ በኋላ ፡ ባለው ፡ በ፫፮ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ግብፅን ፡ ከሚገዙት ፡ ከነበጥሊሞስ ፡ ቤተ ፡ መንግሥትና ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ከሮማውያኖቹ ፡ ውስጥ ፡ አገር ፡ ለማየት ፡ ንግድ ፡ ለማግኘት ፡ የአገር ፡ ካርታና ፡ ታሪክ ፡ ልማድና ፡ ባሕል ፡ ለማጠራቀም ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ጠረፍ ፡ እየመጡ ፡ ሲመለሱ ፡ የተዉትን ፡ ጽሑፍ ፡ ወደ ፡ መመርመር ፡ ይሄዳሉ ።

የነዚህም ፡ የጥንት ፡ ጸሐፊዎች ፡ ያብዛኞቹ ፡ ስም ፡ ኤራስቲን ፤ አናሲክራት ፤ አጋታርሺድ ፡ ጥሊን ፤ ስትራቦን ፤ ሲምኒድ ፡ ዲዮዶር ፤ አርቲሚዶር ፤ ቶሎሜ ፤ ከስማስ ..... ይባላል ፡ እነሱም ፡ ግማሾቹ ፡ የግሪክ ፡ ግማሾቹ ፡ የሮማ ፡ የቀሩትም ፡ የግብፅ ፡ ተወላጆች ፡ ናቸው ። እነዚህም ፡ የኤርትራን ፡ ባሕር ፡ ዞረው ፡ በያገሩም ፡ ተገዝው ፡ ያዩትን ፡ የተረዱበት ፡ መጽሐፍ ፡ ፔሪፕሉ ፡ ማሬ ፡ ኤሪትሬዎ ፡ ይባላል ። ትርጓሜውም ፡ በኤርትራ ፡ ባሕር ፡ ዙሪያ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ እንደዚሁም ፡ የስትራቦንና ፡ የቶሎሜ ፡ ጽሑፍ ፡ ያገር ፡ ካርታና ፡ ያገር ፡ ልማድ ፡ ጭምር ፡ ይተርክል ። በነዚህ ፡ ጸሐፊዎች ፡ አጠራር ፡ በአሁኒቱ ፡ ኢትዮጵያና ፡ በቀድሞዪቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ (ኑብያ) ፡ በያለበት ፡ በነገድ ፡ በቋንቋ ፡ እየተለያየ ፡ ለተቀመጠው ፡ ሕዝብ ፡ ወደ ፡ ዝርዝር ፡ ገብተው ፡ ስም ፡ ሲሰጡ ፡ በኤርትራ ፡ ባሕር ፡ ዳር ፡ በረኻሙ ፡ ያለውን ፡ ሕዝብ ፡ በዋሻ ፡ ነዋሪ ፡ (ትሮግሎዲት) ፤ በዓባይ ፡ ዳር ፡ የሚኖሩትን ፡ ስሆን ፡ በሊቃ ፡ (ስትሩቲአፋኾር) ፤ የቀረውንም ፡ በሚመገበው ፡ ምግብ ፡ ዓይነት ፡ የመልኩ ፡ ቅርጽ ፡ በሚሰጠው ፡ ዓይነት ፡ ዓሣ ፡ በሊቃ ፤ ቀጭኔ ፡ መሰይ ፡ እያሉ ፡ ሠይመውት ፡ ይገኛል ። የዚህን ፡ ዝርዝር ፡ ጉዳይ ፡ ወደፊት ፡ ባለው ፡ ምዕራፍ ፡ ፫ ፡ ላይ ፡ ስለምናገኘው ፡ አሁን ፡ ወደ ፡ ዋናው ፡ ጉዳይ ፡ እንመለስ ።

እነዚህን ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ጸሐፊዎች ፡ ወደጐን ፡ ትተን ፡ ያገራችን ፡ ጽሑፍ ፡ አገራችንን ፡ ወይም ፡ ያገራችንን ፡ ሕዝብ ፡ ምን ፡ እንደሚለው ፡ የተመለከትን ፡ እን ደሆነ ፡ የቀረውን ፡ እንኳን ፡ በየአጋጣሚው ፡ መንከቱ ፡ ሰይቀር ፡ አብዛኛ ፡ ጊዜ ፡ ደጋግሞ ፡ ሲጠራ ፡ የምናገኘው ፡ የመዠመሪያውን ፡ ሕዝብ ፡ ነገደ ፡ ኩም ፡ በኋላ ፡ የመጣውን ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ከባዕድ ፡ ግዛት ፡ ራሱንም ፡ ነገደ ፡ ከሙንም ፡ አወጣው ፡ ለማለት ፡ ነገደ ፡ አግዓዚ ፡ አግዓዝያን ፤ አገሩን ፡ ብሔረ ፡ አግዓዚ ፡ ቋንቋውን ፡ ልሳነ ፡ ግዕዝ ፡ ሲለው ፡ እናገኛለን ።

ዓረብ ፡ መታወቅ ፡ ከዠመረ ፡ በኋላ ፡ በንግግሩም ፡ በጽሕፈቱም ፡ ሐበሻ ፡ (ድብልቅ) ፡ ብሎን ፡ ይገኛል ፡ ግማሹ ፡ ደግሞ ፡ ከደቡብ ፡ ዓረብ ፡ ከነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ከሰባ ፡ ክፍል ፡ አንዱ ፡ ነገድ ፡ ሀበሳት ፡ የሚባለው ፡ የኤርትራ ፡ በሕርን ፡ ተሻግሮ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሰሜን ፡ ስለተቀመጠ ፡ ሐበሻ ፡ የሚባለው ፡ ሥያሜ ፡ የመጣው ፡ ከነ ርሱ ፡ ነው ፡ የሚሉ ፡ አዋቂዎች ፡ ሞልተዋል ። ከዚህ ፡ በፊት ፡ ስማቸውን ፡ የጠቀ ስነው ፡ ምስተር ፡ ሪክማን ፡ (J. RYCKMANS) የሰባውያን ፡ ታሪክዊ ፡ ጽሑፍ ፡ በሚባለው ፡ መጽሐፋቸው ፡ እንደሚያስረዱት ፡ በዛሬው ፡ የመን ፡ ምዕራብ ፡ የሚገ ኘው ፡ ያገሩ ፡ ስም ፡ ሀበሳት ፡ ሰዎቹ ፡ ሀበሳን ፡ የሚባሉት ፡ ሀበሳ ፡ ከሚባል ፡ የነገድ ፡ አባት ፡ የወረዱ ፡ ከአገራቸው ፡ ከደቡብ ፡ ዓረብ ፡ ተሻግረው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ስሜን ፡ ተቀምጠው ፡ ሀበሻ ፡ የሚባለው ፡ ስም ፡ የመጣው ፡ ከነርሱ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ከሌሎቹ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ጋር ፡ ያረጋግጣሉ ። ፓሪስ ፡ በነበርሁ ፡ ጊዜ ፡ በሶርቦን ፡ የምሥራቅ ፡ ቋንቋ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ አማርኛ ፡ ከሚያስተምሩት ፡ ሊቅ ፡ ከማር ሴል ፡ ከሄን ፡ ጋር ፡ የዚህኑ ፡ ጉዳይ ፡ አንሥተን ፡ ስንነጋገር ፡ እናንተ ፡ ኢትዮጵያ ውያን ፡ ሀበሾች ፡ ሲሏችሁ ፡ ቅር ፡ ይላችኋል ፡ ማለትን ፡ ሰምቻለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ እውነተኛ ፡ ስማችሁ ፡ ሀበሻ ፡ መሆኑ ፡ አይጠረጠርም ፡ ያሉኝን ፡ አስታውሳለሁ ። ይኸንንም ፡ ከማለት ፡ ያደረሳቸው ፡ ሀበሳን ፡ ከአገራቸው ፡ ከሀበሳት ፡ (ደቡብ ፡ ዓረብ ፡) መጥተው ፡ በኢትዮጵያ ፡ መቀመጣቸው ፡ እነርሱም ፡ ከነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ መሆናቸውን ፡ በሳባውያን ፡ ፊደል ፡ ሰ ፡ የነበረው ፡ በኋላ ፡ በዓረብኛ ፡ ሰ ፡ ወደ ፡ ሸ ፡ ተለውጦ ፡ ሀበሻ ፡ ስንባል ፡ የኖርነውን ፡ ደንበኛ ፡ ታሪክ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ነው ።

በብሉይ ፡ ኪዳን ፡ በዘፍጥረት ፡ ምዕራፍ ፡ ፲ ፤ በኖኅ ፡ ዘር ፡ ውስጥ ፡ ሁለት ፡ ሰባ ፡ እንዳለ ፡ ዘጥውልዱ ፡ ሐረግ ፡ ላይ ፡ እንመለከታለን ። አንደኛው ፡ የኖኅ ፡ ልጅ ፡ የካም ፡ የልጅ ፡ ልጁ ፡ የኩሽ ፡ ልጅ ፡ ሰባ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ከሌላው ፡ ለመለየት ፡ ሰባ ፡ ሸባ ፡ ይሉታል ። ይኸም ፡ የካሙ ፡ ነገድ ፡ የኑብያው ፡ ኢትዮጵያ ፡ የነገድ ፡ አባት ፡ መሆኑ ፡ ነው ። በዚህም ፡ ሰባ ፡ ሮባ ፡ እየተባለ ፡ ይጠራል ። የሁለተኛው ፡ ትውልድ ፡ ደግሞ ፡ ኖኅ ፡ የካምን ፡ ወንድም ፡ ሴምን ፡ ሴም ፡ አርፋ ክስድን ፤ አርፋክስድ ፡ ሳላህን ፤ ሳላህ ፡ አቤርን ፤ አቤር ፡ ዮቅጣንን ፤ ዮቅጣን ፡ ሰባን ይወልዳል ። የዚህኛውን ፡ የሰባን ፡ ነገድ ፡ ነው ፡ በደቡብ ፡ ዓረብ ፡ ሲኖር ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መጥቶ ፡ የካምን ፡ ዘሮች ፡ አሸንፎ ፡ ባለቤት ፡ ሆነ ፡ የምንለው ፡

ንግሥት ፡ ሳባም ፡ ነገሥት ፡ የምትባለው ፡ በነዚሁ ፡ ነገዶች ፡ ላይ ፡ ነው ። ሀበሳን ፡ ሳባ ፡ ሂሚያሬት ፡ እየተባለ ፡ መለያየት ፡ የመጣውም ፡ በዘመን ፡ ብዛት ፡ በትውልድ፡ መበርከት ፡ ነው ።

እንግዲህ ፡ የኩሹ ፡ ሳባ ፡ /ሰባ ፡ ሻባ ፡/ ከም ሥራቅ ፡ መጥቶም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ግማሹ ፡ የርሱና ፡ ያባቱ ፡ የካም ፡ ወገኖች ፡ ተደባልቀው ፡ በሁኒቱ ፡ ኢትዮጵያና ፡ በቀድሞዪቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በኑብያ ፡ ሲኖሩ ፡ በኑብያ ፡ ያሉት ፡ ብዙውን ፡ ዘመን ፡ በነፃነት ፡ ከኖሩ ፡ በኋላ ፡ በመጨረሻ ፡ በሺ፩፱፡ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ላይ ፡ በግብፅ ፡ ተገዙ ። በመጨረሻ ፡ ደግሞ ፡ በ፲፯ው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ላይ ፡ እነዚሁ በግብፅ ፡ የተገዙት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ መልሰው ፡ ግብፅን ፡ ገዙ ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ በሁኒቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሚገኙት ፡ አግዓዚ ፡ ወይም ፡ ኃበሳን ፡ የሚባሉት ፡ ሲመጽ፡ው ፡ በነፃነት ፡ ሳይመጽ፡ው ፡ ግብፅ ፡ በፊት ፡ ናፖኦ ፡ በኋላ ፡ በየጊዜው ፡ እየወረሯ፡ውና ፡ እየገበሩ ፡ በመከከላ፡ው ፡ ኃይለኛ ፡ ሲነሣ ፡ እየጠቀለላ፡ው ፡ ሲጠ ፉም ፡ በየነገዳ፡ው ፡ እየተከፋፈሉ ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ እስከ ፡ መቶ ፡ ወይም ፡ ቢበዛ ፡ ፪ ፡ መቶ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ኖሩ ። በኋላ ፡ ግን ፡ በግብፅና ፡ በኖ ብያ ፡ የአሶር ፤ የፋርስ ፤ የግሪክ ፤ የሮማ ፡ ገዥ ፡ እየተፈራረቀ ፡ የኖብያው ፡ የኢት ዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ሲደክም ፡ በጐኑ ፡ ያለው ፡ የሀበሳት ፡ ወይም ፡ የአግዓዝያን ፡ ሕዝብ ፡ የአክሱምን ፡ መንግሥት ፡ እያቀና ፡ ተነሣ ። ስለዚህ ፡ ይህን ፡ መንግሥት የሮማና ፡ የቢዛንቲን ፡ ጸሐፊ ፡ ሁሉ ፡ በያውራጃው ፡ ለሚገኘው ፡ ሕዝብ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ስም ፡ መስጠቱ ፡ ሳይቀር ፡ ዋነኛውን ፡ መንግሥት ፡ አክሱም ፡ መሥርተው ፡ ጽሕፈት ፡ ሲያስቀርጹ ፡ ንጉሡ ፡ የአክሱም ፡ ንጉሥ ፡ ሕዝቡም ፡ አክሱማውያን ፡ እየተባሉ ፡ አገሩም ፡ ብሔረ ፡ አኵስም ፡ በሚል ፡ ይጠራ ፡ ገሞር ፡ ይሁን ፡ እንጂ ይህ ፡ ግዕዝኛ ፡ አነጋገር ፡ የመጣ ፡ ከክርስትና ፡ በኋላ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የፊተኛው ፡ አነጋገርና ፡ ጽሑፍ ፡ ቀድሞ ፡ ብደቡብ ፡ ዓረብ ፡ ሰሉ ፡ የሚጽፉበትና ፡ የሚነጋገሩ በት ፡ የሳባ ፡ ቋንቋ ፡ ነው ። ይኸም ፡ የሳባ ፡ ፊደልና ፡ ቋንቋ ፡ ለግዕዙ ፡ እንደ ፡ አባት ፡ የሚቆጠር ፡ ነው ። ደግሞ ፡ በአክሱመ ፡ መንግሥት ፡ የግሪክ ፡ ቋንቋ ፡ ሲሰ ለጥን ፡ በየሐውልታ፡ው ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በሳባያውያን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በግ ሪክ ፡ ቋንቋ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ባልሠለጠነው ፡ ግዕዝኛ ፡ ወይም ፡ ሁለቱን ፡ ግሪኩ ንና ፡ ሳባውን ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ እያደረጉ ፡ ሲያጽፉ ፡ የነበረው ፡ እነሆ ፡ ዛሬ ፡ በየሃ ውልታ፡ው ፡ ላይ ፡ ይታያል ። በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ከክርስትና ፡ በኋላ ፡ የተጻፈው ፡ ሁሉ እላይ ፡ እንዳልነው ፡ ብሔረ ፡ አክሱም ፡ ንጉሠ ፡ አክሱም ፡ አክሱማውያን ፡ ሲል ፡ ይገኛል ። ይኸም ፡ ሥያሜ ፡ በዘመኑ ፡ ይኸው፡ም ፡ ማለት ፡ በአክሱሞቹ ፡ ዘመን ፡ የኢ ትዮጵያዊነትን ፡ ይልቁንም ፡ የሳባንና ፡ የሀበሳትን ፡ ሥያሜ ፡ እያጠፋው ፡ ሳይሆን ፡ እያደበዘዘው ፡ ሔዷል ።

እያንዳንዱ ፡ ሕዝብ ፡ በጊዜውና ፡ በሥፍራው ፡ በነገዱ ፡ የየራሱን ፡ ከተማ፡ ስም፡ ናፖኦ ፡ መርዊ ፡ አክሱም ፡ እያለ ፡ ይኸንኑ ፡ ስም ፡ በማድመቁ ፡ ጸሐፊም ፡ በዚሁ እየሠየመው ፡ የዋናውን ፡ የጥንታዊውንና ፡ የጠቅላላውን ፡ የኢትዮጵያዊነት ፡ ስም፡

ሊዘነጋ ፡ ምንም ፡ አልቀረውም ፡ ነበር ። ከጸሐፊዎችም ፡ አንዳንዶቹ ፡ ለወዲህኛው ፡ በፊት ፡ የሀበሳትን ፡ በኋላም ፡ የአክሱምን ፡ ስም ፡ እየሰጡ ፡ ኢትዮጵያነትን ፡ ለኩ ፡ ብያ ፡ /ለናፓታና ፡ ለመርዌ/ ፡ የሚሰጡ ፡ አሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ እንደሐሜርም ፡ እንደ ሄሮዱትም ፡ ቢሆን ፡ የኢትዮጵያዊነት ፡ ስም ፡ ለናፓታና ፡ ለመርዌ ፡ ብቻ ፡ ሊወሰን ፡ አይገባም ። በዚሁ ፡ መሠረት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ስም ፡ በሌላው ፡ ክፍል ፡ መብረድ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በፍጹም ፡ ሲጠፋ ፡ በኛ ፡ በዛሬዩቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከፓያና ፡ ከሠፓ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ወዲህ ፡ መንግሥት ፡ ከአክሱም ፡ ላስታ ፡ ከላስታ ፡ ሸዋ ፡ ከሸዋ ጐንደር ፡ በተዛወረበት ፡ ጊዜ ፡ . . . . ሐበሻ . . . የሚባለው ፡ ስም ፡ ጣልቃ ፡ መግባቱ ፡ ባይቀርም ፡ አብዛኛ ፡ ጊዜ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሥያሜ ፡ በዜና ፡ መዋዕልም ፡ በገድልና ፡ በድርሳንም ፡ በደብዳቤም ፡ እንደገና ፡ ይነሣ ፡ ገሾመር ። በሠፓ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ላይ ፡ የነበረው ፡ ድልነዓድ ፡ /እንደሌሎቹም ፡ ሠይፈ ፡ አርዕድ ፡ ለኖብ ያው ፡ ንጉሥ ፡ ለጊዮርጊስ ፡ ደብዳቤ ፡ በግዕዝ ፡ ቋንቋ ፡ ሲጽፍ ፡ ስሙን ፡ ሳይጠ ቅስ ፡ ንጉሠ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ብሏል ። የላሊበላና ፡ የነአኩቶ ፡ ለአብ ፡ የዓምደ ፡ ጽዮ ንና ፡ የዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ታሪክ ፡ ነገሥትም ፡ እያንዳንዳቸውን ፡ ንጉሠ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሲላቸው ፡ ይገኛል ።

ከውጭ ፡ አገር ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ውስጥ ፡ የሮማ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ አራተኛው ፡ ፓውሊ ፡ /ጳውሎስ/ ፡ በፊሺ ፡ ፫፪ ፡ ፱፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ለአፄ ፡ ገላውዴዎስ ፤ ፊልጶስ ፡ ፪ ፡ የኤስፓኝ ፡ንጉሥ ፡ ለአፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ደብዳቤ ፡ በላቲን ፡ ቋንቋ ፡ ሲጽፉ ፡ IMP - ERATOREM AETHIOPIAE የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ እያሉ ፡ የጻፉት ፡ በካሪ ፡ በሰበሰበው ፡ የፖርቱጌዝና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ግንኙነት ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ተመዝ ግቦ ፡ ይገኛል ።

ስለዚህ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ስም ፡ ጥንት ፡ በሰፊው ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ አቅፎ ፡ ቢገ ኝም ፡ ግሪክቹ ፡ እነሐሜር ፡ እነሄሮዱቱስ ፡ እስራኤሎቹ ፡ እነዳዊት ፡ እነኢሳይያስ ፡ የመሠረቱትን ሥያሜ ፡ ሳይለቅ ፡ ኩሽ ፤ ሐበሻ ፡ በዋሻ ፡ ነዋሪ ፡ የሚባለውን ፡ ሁሉ ፡ ደም ስሶ ፡ በአሁኑ ፡ ዘመን ፡ በፖለቲካና ፡ በወሰን ፡ ተከልሎ ፡ አሁን ፡ ላለው ፡ ሕዝባ ችን ፡ ኢትዮጵያዊነት ፡ የግሉ ፡ መጠሪያ ፡ ሆኖ ፡ መቅረቱን ፡ እንመለከታለን ። ይኸም ፡ ሲሆን ፡ የሳባውያን ፡ የሀበሳን ፡ ነገድ ፡ ዘሮች ፡ መሆናችንን ፡ ሳንረሳ ፡ ሀበሻ ፡ መባ ልንም ፡ ሳንጠላ ፡ ነው ።

ም ዕ ራ ፍ ፪ ።

የቀድሞው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጽሑፍ ፡ ሁኔታ ።

የአክሱሙ ፡ መንግሥትና ፡ ሕዝብ ፡ ከደቡብ ፡ ዓረብ ፡ ሕዝብ ፡ ታሪክ ፡ ከፊ ደሉ ፡ ከሥልጣኔው ፡ ከልማዱ ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ እንደሆነ ፡ እንዲሁም ፡ ያንጊዜ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወይም ፡ የኩሽ ፡ አገር ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራው ፡ የኑብያ ሕዝብ ፡ የሥ ልጣኔው ፡ መደብ ፡ በናፓታና ፡ በመርዌ ፡ የነበረው ፡ በሃይማኖትም ፡ በሥልጣኔም

በልማድም ፡ ከግብፅ ፡ ሕዝብ ፡ የተገናኘ ፡ ነበር ። ባጭሩ ፡ የተገናኘ ፡ ነው ፡ ከማ ለት ፡ ይልቅ ፡ የኑብያው ፡ ሕዝብ ፡ ሬደሉና ፡ ሃይማኖቱ ፡ የዋነኞቹና ፡ የሥልጡ ኖቹ ፡ ወገኖች ፡ የግብፅ ፡ ሬደል ፡ (ሂዬሮግሊፍ ፡) የሚባለው ፡ ነበር ። በሃይማኖ ትም ፡ ረገድ ፡ የግብፃውያንን ፡ አማልክት ፡ እነአሞንን ፡ ያመልኩ ፡ ነበር ። ተራው ፡ ባለገር ፡ ደግሞ ፡ ከግብፅ ፡ ባላገር ፡ ከወዲህም ፡ ከዘሬዱቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ባላገር ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ከፍጡራን ፡ የመነጨ ፡ የፍጡርና ፡ የመናፍስት ፡ አም ልክ ፡ ነበረው ።

ስለዚህ ፡ በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ አክሱም ፡ ሲገን ፡ / ሲነማ ፡ / ሃይማኖትንና ፡ ሬደልን ፡ ከደቡብ ፡ ዓረብ ፡ ይዘ ፡ የመጣውን ለዛሬው ፡ ሬደላችን ፡ አባት ፡ የሆ ነውን ፡ የሳባውያንን ፡ ሬደል ፡ በግዛቱ ፡ ስለአስፋፋ ፡ በኋላም ፡ ይኸው ሬደልና ፡ ቋንቋ ፡ ወደ ፡ ግዕዝ ፡ ተለውጦ ፡ ዛሬ ፡ ጽሑፉ ፡ ሁሉ ፡ በዚያው ፡ በመጠኑ ፡ ስለአክሱም ፡ መንግሥት ፡ ሲናገር ፡ ኑብያን ፡ እንደባዕድ ፡ በመመልከት ፡ በጉ ዳዩ ፡ ሳያገባው ፡ ቀርቶ ፡ ገዛነው ፡ አስገበርነው ፡ ብሎ ፡ ከማለፍ ፡ በቀር ፡ ስለ ኑብያ ፡ መንግሥት ፡ ሁኔታ ፡ በሰፊው ፡ የሚናገር ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ የለም ። የኑብያውም ፡ በናፓታና ፡ በመርዌ ፡ የተፈጸመው ፡ በሂዬሮግሊፍ ፡ የተጻ ፈው ፡ ታሪኩ ፡ እንደቱበና ፡ እንደመምሬስ ፡ ታሪክ ፡ ተደብቆ ፡ ሲኖር ፡ ሻምፖል የን ፡ የሬደሉን ፡ ምሥጢር ፡ ከፈታው ፡ ወዲህ ፡ ብዙ ፡ መርማሪዎች ፡ ጥንታ ዊውን ፡ የግብፅን ፡ ታሪክ ፡ እየመረመሩ ፡ ሲያወጡ ፡ የኑብያውም ፡ ታሪክ ፡ እየተመረ መረ ፡ መውጣት ፡ ዠመረ ። ኑብያን ፡ ከግብፅ ፡ ጋር ፡ ደርበው ፡ ሲገዙ ፡ የኖሩት ፡ ፈርዖኖች ፡ እንደገና ፡ ኢትዮጵያውያኑ ፡ ደግሞ ፡ ከኑብያ ፡ ተነሥተው ፡ ግብ ፅን ፡ በሙሉ ፡ አስከ ፡ ሊቢያ ፡ አስከፓለስቲን ፡ የገዙት ፡ የግብፅ ፡ ጀግኖ ፡ ሥርወ ፡ መንግሥት ፡ (ዲናስቲ) ፡ ተብለው ፡ የተመደቡት ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ ንገሥታት ፡ የነፒያንኪ ፡ የነታርሐቃ ፡ ታሪክ ፡ ክሐውልትና ፡ ከጣያታቱ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ግድግዳ ፡ ላይ እየተተረጐመ ፡ ይወጣ ፡ ዠመር ። ይኸንንም ፡ ወደ ፊት ፡ በሥፍራው ፡ ስንደርስ ፡ እናገኘዋለን ።

የሆነ ፡ ሆኖ የኢትዮጵያ ፡ የጥንታዊ ፡ ግዛት ፡ ነበር ፡ አስቀድሞ ፡ ሲገዙ ፡ ቢኖሩም ፡ በኋላ ፡ መልሰው ፡ ግብፅን ፡ ገዝተዋል ፡ እያልን ፡ ስለምንመካባቸው ፡ ስለ ፡ ኑብያ ፡ ሕዝቦች ፡ በተለይ ፡ ስለናፓታና ፡ ስለመርዌ ፡ ደንበኛ ፡ ታሪክ ፡ የሚናገር ፡ ስግዕዝም ፡ በአማርኛም ፡ የተጻፈ ፡ ብዙ ፡ የለም ። በየሐንስ ፡ መደብር ፡ ስለ ስባቆን ፡ (ሽባክ) ፡ ስለ ፡ ንግሥት ፡ ሕንደኬና ፡ ስለ ፡ ትልቁ ፡ እስክንድር ፡ ግንኙነት ፡ በቲንሹ ፡ ሰኖር ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ ያለው ፡ ሰፊ ፡ የኑብያ ፡ መንግ ሥት ፡ ታሪክ ፡ ለዚያን ፡ ዘመንም ፡ ለዛሬዬቱም ፡ ኢትዮጵያ ፡ የተጀፈነ ፡ ጨለማ ፡ ነው ። የዚህ ፡ የኑብያ ፡ ታሪክም ፡ እላይ ፡ እንዳመለከትነው ፡ ከና ፓታና ፡ ከመርዌ ፡ ዝቅ ብሎም ፡ ከቱብ ፡ (ካርናቅ) ፡ ከዙሪያውም ፡ ከየሀውልቱና ፡ ከየመቅደሱ ፡ ከቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ፍራሽ ፡ ቢገኝም ፡ በግብያቹ ፡ ጥንታዊ ፡ ሬደል ፡ የተጻፈ ፡ ሆኖ ፡ የሚተርከውም ፡ ስለ ፡ ኑብያ ፡ ይኸውም ፡ ማለት ፡ የናፓታ

ንና ፡ የመርዌን ፡ መንግሥት ፡ እንጂ ፡ አሁን ፡ ከያዝነው ፡ ፈደልና ፡ ታሪክ ፡ ጋራ ፡ ተመራራሽ ፡ ስለሆነው ፡ ስለአክሱም ፡ አይናገርም ። በዘርና ፡ በአንዳንድ ፡ ልማድ ፡ ከልሆነ ፡ በቀር ፡ የኑብያው ፡ ሥልጣኔና ፡ ታሪክ ፡ ሃይማኖቱም ፡ ከአክሱም ፡ ሥልጣኔ ፡ ጋር ፡ የማይገናኝ ፡ ነው ። ቢባልና ፡ የኑብያውን ፡ ችላ ፡ ብንልም ፡ ስለራሱ ፡ ስለአክሱም ፡ መንሥት ፡ ታሪክ ፡ እንኳን ፡ በታሪክ ፡ ነገሥትም ፡ በክብረ ፡ ነገሥትም ፡ በብዕለ ፡ ነገሥትም ፡ በነገሥታቱና ፡ በጳጳሳቱ ፡ ድርሳንና ፡ ገድል ፡ ውስጥ ፡ የተጻፈውም ቢሆን ፡ በደረቅ ፡ ታሪክ ፡ ረገድ ፡ የሚሰጠን ፡ ጥቅም ፡ ዝቅ ፡ ያለ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ዛሬ ፡ የሚገኘው ፡ ይኸን ፡ የመሳሰለው ፡ ጽሑፍ ፡ የጥንቱ በዮዲትና ፡ በግራኝ ፡ መሐመድ ፡ መነሣትና በሌላውም ፡ ምክንያት ፡ ጠፋፍቶ ፡ እንደገና ፡ መዘጋጀት ፡ የቻለው ፡ ከ፲፬ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ወዲህ ፡ ከአፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ በመሆኑ ፡ ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ ሞላ ፡ ከገዳል ፡ የመንግሥትም ፡ የመንፈሳዊም ፡ ታሪክ ፡ ይገኛል ። ግልባጩ ፡ ሳይሆን ፡ አንዳንድ ፡ መንፈሳዊ ፡ ጽሑፍ ፡ በይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ጊዜ ፡ የተዘጋጀ ፡ አለ ፡ ከዚሁ ፡ ጀምሩ ፡ ብሔረ ፡ አሪት ፡ የሚባለው ፡ ዛሬ ፡ በፓሪስ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ የሚገኘው ፡ እንደብርቅ ፡ ይታያል ።

ከዓፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ያለፈውን ፡ የላስታና ፡ ይልቁንም ፡ የአክሱምን ፡ ታሪክ ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ሰዎች ፡ መነኮሳትና ፡ እፈጌዎች ፡ የመንግሥቱም ፡ ጸሐፊዎች ፡ ሲያያገ ፡ በመሬ ፡ የመጣውን ፡ ከራሳቸውም ፡ እየጨመሩ ፡ ሲያዘጋጁ ፡ ለያንዳንዱ ፡ የአክሱምና ፡ የላስታ ፡ ንጉሥ ፡ በዘመኑ ፡ የፈጸመውን ፡ አጫጭር ፡ የጦርነትና ፡ የመንፈሳዊ ፡ ተግባር ፡ ሲያዘጋጁ ፡ በየዘመኑ ፡ የነበረውን ፡ ልማድና ፡ አስተዳደር ፡ የዕቃና ፡ የመሣሪያ ፡ የሽቀጥና ፡ የገንዘቡን ፡ ዓይነት ፡ ሌላውንም ፡ ይኸን ፡ የመሳሰለውንም ፡ ጽፈው ፡ ለማቅረብ ፡ የዘመኑ ፡ የጸሐፊነት ፡ ልማድ ፡ አላስቻላቸውም ። ጽፈው ፡ ጠፍቶም ፡ እንደሆነ ፡ አይታወቅም ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ የዚህ ፡ ሁሉ ፡ ዓይነት ፡ በደንብና ፡ በዝርዝር ፡ ተጽፎ ፡ ወደ ፡ ጊዜያችን ፡ የተላለፈ ፡ አላገኘንም ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ፈረንጆች ፡ የሩን ፡ የሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ደረጃ ፡ ከጓደኞቻችን ፡ አገሮች ፡ ከዓረብና ፡ ከግብፅ ፡ ከፋርስና ፡ ከግሪክ ፡ በዝቅ ፡ ተኛነት ፡ ለመገመት ፡ ግዴታ ፡ ሆኖበቸዋል ።

በዚሁ ፡ ባለን ፡ ታሪክ ፡ ነገሥት ፡ ውስጥ ፡ እንደምንመለከተው ፡ ከአዳም ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዳዊት ፡ ከሰሎሞን ፡ እስከ ፡ ይኩኖ ፡ አምላክ ፡ የስም ፡ ዝርዝር ፡ ይሰጥና ፡ ከዚያ ፡ ጣልቃ ፡ እያገባ ፡ የንግሥቲ ፡ ሳባንና ፡ የሰሎሞንን ፡ ግንኙነት ፡ የቀዳማዊ ፡ ምኒልክን ፡ ልደትና ፡ ንግሥ ፤ የአብርሃንና ፡ የአጽብሐን ፡ ቲንሽ ፡ ታሪክ ፡ ከአቡነ ፡ ሰላማ ፡ (ከሣቴ ፡ ብርሃን) ፡ ጋር ፤ ያዜ ፡ ከሌብን ፡ ከአባ ፡ ጸንጠሌዎን ፤ ያዜ ፡ ገብረ ፡ መስቀልን ፡ ከያሬድና ፡ ከአቡነ ፡ አረጋዊ ፡ ጋር ፡ እያያያዘ ፡ ይጽፋል ። ከዚያ ፡ የላሊበላንና ፡ የነአኩቶ ፡ ለአብን ፡ የይኩኖ ፡ አምላክንና ፡ የአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ይተርክል ። አተራረኩም ፡ በደረቅ ፡ ታሪክና ፡ ወይም ፡

ለታሪኩ ፡ ብቻ ፡ ቀጥተኛ ፡ ሐተታ ፡ በመስጠት ፡ ሳይሆን ፡ በመንፈሳዊና ፡ በተአምራታዊ ፡ አገላለጽ ፡ ሆኖ ፡ እናገኘዋለን ። ይኸም ፡ እንደማናቸውም ፡ ሥራ ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ የተለመደና ፡ የማያስነቅፍ ፡ ነው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ እላይ ፡ እንዳመለከትነው ፡ ያብዛኞቹ ፡ ነገሥታት ፡ ከስማቸው ፡ ዝርዝር ፡ በቀር ፡ በዕለት ፡ ተግባራቸው ፡ የፈጸሙት ፡ የፍርዱ ፡ የሥርዓቱ ፡ የጦርነቱ ፡ የንግዱ ፡ አኳኋን ፡ የሸቀጡ ፡ የጦር ፡ መሣሪያው ፡ ለኑሮና ፡ ለትዳር ፡ ወንዱና ፡ ሴቱ ፡ የሚገለገሉበት ፡ ዕቃና ፡ መሣሪያ ፡ በአማርኛ ፡ እንኳ ፡ ተስፋ ፡ ለማድረግ ፡ የራሱ ፡ የቋንቋው ፡ አለመኖር ፡ አያስችልም ፡ ብንል ፡ በዘመኑ ፡ በሚሠራበት ፡ በቤተ፡ መንግሥቱና ፡ በቤተ ፡ ክህነቱ ፡ ቋንቋ ፡ በግዕዝ ፡ እንኳ ፡ አይገኝም ። ባንዳንድ ፡ ቦታ ፡ በብርቅ ፡ ቢገኝም ፡ በጣም ፡ ያነሰ ፡ ከግማሽ ፡ ገጽ ፡ ስለማይደርስ፡ ለዛሬ ፡ ዘመን ፡ ጸሐፊና ፡ አንባቢ ፡ የማያጠግብ ፡ ይሆናል ።

ክርስትናን ፡ ጌታችን ፡ ከመሠረተው ፡ ሐዋርያትና ፡ ሰማዕታት ፡ በያለበት ፡ ካስፋፉትና ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያም ፡ አባ ፡ ሰላማ ፡ ፍሬምናጦስ ፡ ካገቡት ፡ ወዲህ፡ እንደዛሬው ፡ ዘመን፡ ልማድ፡ እላይ፡ የዘረዘርነውን፡ ያገር ፡ ልማድ ፡ የዕቃና ፡ የመሣሪያ ፡ ዓይነት፡በዝርዝር ፡ ለመጻፍ ፡ አባቶቻችን ፡ አሰባቸውን ፡ ማድከም ፡ አልፈለጉም ። ዛሬ ፡ የፈለግነውን ፡ ያህል ፡ ለኋላ ፡ ትውልድ ፡ ይጠቅመዋል ፡ ብለው ፡ ያን ፡ ጊዜ፡ እምብዛም ፡ የተገነዘቡት ፡ አይመስልም ። በዚህ ፡ ፈንታ ፡ ስለ ፡ አዲሱ ፡ የክርስትና ፡ ሃይማኖት ፡ ስለሐዋርያትና ፡ ስለሰማዕታት ፡ ስለመላእክቱና ፡ ስለጻድቃን ፡ ከነዚሁ ፡ ጋር ፡ ስለተያያዙት ፡ ነገሥታት ፡ በመንፈሳዊ ፡ አያያዝ ፡ ብቻ ፡ ለመጻፍና ፡ ለመድከም ፡ የዘመኑ ፡ ጸሐፊዎች ፡ የሆኑት ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ሰዎች፡ አሰባቸውን ፡ በሙሉ ፡ ወደዚህ ፡ ሥራ ፡ አዘነበሉ ። የማይካደውን ፡ ትጋታቸውንና ፡ ዕውቀታቸውን ፡ ለዚሁ ፡ ለመንፈሳዊ ፡ ጽሕፈት ፡ ሠዉት ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ እነሆ ፡ ዛሬ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ መንግሥትና ፡ ቤተ ፡ ክህነት ፡ በገዳማትና ፡ በየአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ውስጥ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ መጻሕፍት ፡ ሁሉ፡ የገድል ፡ የድርሳን ፡ የመልክ ፡ መልክ ፡ የጸሎት ፡ የምነና ፡ መጻሕፍት ፡ በጥሩ፡ ጥሩ ፡ ብራና ፡ በሚያማምር ፡ ጽሕፈትና ፡ ድጉስ ፡ በደመቁ ፡ ሐረጎች ፡ አጊጦ ፡ ሲገኝ ፡ የታሪኩ ፡ የመሣሪያውና ፡ የዕቃው ፡ የሥርዓቱ ፡ ጽሑፍ ፡ አንሰና ፡ ጐድሎ ፡ ይገኛል ። አባቶቻችን ፡ ይኸኛውን ፡ ሥራ ፡ ወደሚያልፍ ፡ ወደሥጋዊ ፡ ወደምድራዊ ፡ ስለቆጠሩት ፡ መንፈሳዊ ፡ መጽሐፍ ፡ ብቻ ፡ አበረከቱልን ።

ስለዚህ ፡ የታሪኩ ፡ ወገን ፡ በዚያው ፡ ዘመን ፡ ችላ ፡ ስለተባለ ፡ ዛሬ ፡ ታሪክ ፡ እያለን ፡ የታሪክ ፡ ደሀ ፡ ሆነን ፡ ስንኖር ፡ እኛም ፡ ራሳችን ፡ በራሳችን ፡ የራሳችንን ፡ ታሪክ ፡ ቆፍረን ፡ እንኳን ፡ ባይሆን ፡ ከቆመው ፡ ሐውልት ፡ ላይ ፡ ለመገልበጥና፡ለመረዳት ፡ ስለአቃተን ፡ ወይም ፡ ስለአላሰብንበት ፡ የዚህ ፡ ሥራ ፡ ልማድ ፡ ያላቸው ፡ ለታሪክ ፡ ዋጋ ፡ መስጠት ፡ የቻሉ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ አፍሪካን ፡ ለማየት ፡ አደን ፡ ለማደን ፡ ታሪክ ፡ ለመመርመር ፡ በየምክንያቱ ፡ ካገራቸው ፡ ሲወጡና ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሲመጡ ፡ በአክሱምና ፡ በዙሪያው ፡ ከለው ፡ ሐውልት ፡ ላይ ፡ አንዳንድ ፡

ጽሑፍ ፡ እየቀዱ ፡ እየተረጎሙ ፡ የታሪካችንን ፡ ብልጫታ ፡ አሳዩን ። እነዚህም ፡ እንደ ነጅምስ ፡ ብሩስ ፤ ኤድዋርድ ፤ ሩፔል ፤ ሀንሪ ፡ ሳልት ፤ ከንቲ ፡ ሮሲኒና ፤ ሌሎችም ፡ ናቸው ። እነሱም ፡ እየተነጣጠሉ ፡ የተቻላቸውን ፤ ለየብቻ ፡ በጽሑፍ ፡ ገልጸው ፡ ከቆዩ ፡ በኋላ ፡ ፲፱፻፲ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሰሜን ፡ ጸሐፊ ፡ ፎቶግራፍ ፡ አንሺ ፡ ቆሩሪ ፡ ፕላን ፡ ሠሪ ፡ ሆነው ፡ ባንድ ፡ ጓድ ፡ የመጡት ፡ እነሊትማን ፡ በአክሱምና ፡ በሌላም ፡ ታሪካዊ ፡ ሥፍራ ፡ እየተዘዋወሩ ፡ ቆሞና ፡ ወድቆ ፡ ካገኙት ፡ ሐውልት ፡ ላይ ፡ ያገኙትን ፡ የሳባ ፡ የግሪክ ፡ የግዕዝ ፡ ጽሑፍ ፡ እየቀዱ ፡ ባንዳንድ ፡ ቦታም ፡ በቁፋሮ ፡ እያገኙ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነ ፡ ሥራ ፡ አዘጋጁ ። ደች ፡ አክሱም ፡ ኤክስፔዲሽን ፡ (DEUTSCHE AXUM EXPEDITION) የሚባለውን ፡ በአራት ፡ ቮሉም ፡ በጀርመን ፡ ቋንቋ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ የታተመውን ፡ መጽሐፍ መመልከት ፡ ነው ። የጀርመኑን ፡ ቋንቋ ፡ ለመረዳት ፡ እንደኔ ፡ ያቃተው ፡ ሰው ፡ በአራተኛው ፡ ቮሉም ላይ ፡ ያለው ፡ ከየሀውልቱ ፡ በቀጥታ ፡ የተወሰደውና ፡ የታተመው ፡ የሳባውና ፡ የግዕዙ ፡ ጽሑፍ ፡ ለታሪክ ፡ ጸሐፊ ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ ያገለግላል ።

ከነርሱ ፡ የተረፈውን ፡ ደግሞ ፡ እነሆ ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የፈረንሳዊና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ተወላጆች ፡ የአርኬዎሎሽ ፡ ሠራተኞች ፡ በሕብረት ፡ በአክሱምና ፡ በዙሪያው ፡ እየተፈላለጉ ፡ አንዳንድ ፡ የተነጣጠለ ፡ ታሪካዊ ፡ ዕቃ ፡ ማግኘታቸውን ፡ አይተናልና ፤ ድካማቸው ፡ በመጨረሻ ፡ ፍሬ ፡ አግኝቶ ፡ የተደበቀና ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ የደከሙት ፡ ጸሐፊዎች ፡ ያላገኙት ፡ ጽሑፍ ፡ እንዳለ ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ እንዲያመጡልን ፡ እንመኛለን ።

እስከዚያ ፡ ግን ፡ ሥራ ፡ ሳንፈታ ፡ እስካሁን ፡ ከተገኘው ፡ የሐውልትና ፡ የብራና ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ከገድሉና ፡ ከድርሳኑ ፡ ውስጥ ፡ በትዕግሥት ፡ እየለቀምን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ታሪክ ፡ የዘሬው ፡ ሕዝባችን ፡ በሚናገረው ፡ በአማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ አብራርተን ፡ ለመጻፍ ፡ ዓላማችን ፡ ሆኖ ፡ እነሆ ፡ እማዘጋጅት ፡ ላይ ፡ ነን ፡ ሐውልትና ፡ አጭሩ ፡ ታሪክ ፡ ነገሥት ፡ አብዛኛው ፡ የታሪክ ፡ ክፍል ፡ ሆኖ ፡ ሲያገለግል ፡ ገድሉና ፡ ድርሰኑ ፤ በሙሉ ፡ የሚጽፈው ፡ ያንድ ፡ ጻድቅ ፡ ወይም ፡ መልአክ ፡ ታምራታዊ ፡ ታሪክ ፡ ቢሆንም ፡ ከዚሁ ፡ ከመንፈሳዊ ፡ አንጋፋ ፡ ውስጥ ፡ የመልአኩና ፡ የጻድቁ ፡ ወዳጅ ፤ ንጉሥ ፡ ወይም ፡ ንግሥት ፤ መስፍን ፡ ወይም ፡ መኰንን ፡ ስማቸው ፡ ጣልቃ ፡ እየገባ ፡ ይገኛል ። ያንዳንዱም ፡ ታሪካዊ ፡ ቦታ ፡ ስም ፡ አይጠፋበትምና ፡ እነዚህን ፡ ከየቦታው ፡ አግኝቶ ፡ ለመልቀም ፡ ሰፊውን ፡ መንፈሳዊ ፡ ንግግር ፡ በትዕግሥት ፡ ማንበብ ፡ ግዴታ ፡ ነው ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ሁሉም ፡ ቢሆን ፡ እንደ ፡ ንግሥተ ፡ ሳባና ፡ እንደ ፡ ቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ወይም ፡ እንደ፡አብርሃ፡አጽብሐ ፡ እንደ ፡ ላሊበላና ፡ እንደ፡ይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ላሉት ፡ ከልሆነ ፡ በቀር ፡ አብዛኞቹ ፡ የአክሱም ፡ የላስታ ፡ ነገሥታቶችን ፡ ገድልና ፡ ድርሰን ፡ ያልተጻፈላቸው ፡ ስላሉ ፡ ከስማቸው ፡ ዝርዝር ፡ በቀር ፡ ታሪክቸው ፡ እየተቋረጠ ፡ መቅረቱ ፡ ነው ። የመሳፍንትና ፡ የመኳንንት ፡ ዝርዝር ፡ ማግኘትም ፡ ተስፋ ፡ የለም ። እንኳን ፡ ታሪክቸው ፡ ወደፊት ፡ በሥፍራው ፡ እንደ ፡ ምናስረዳው ፡ የነገሥታቱ ፡ ስማቸውና ፡ የነገሡበት ፡ ዘመን ፡ እየተሳለሰ ፡ ያስቸግራል ።

እንደዚህ ፡ ሆኖ ፡ አሁን ፡ ጥንታዊውን ፡ የኑብያን ፡ መንግሥት ፡ ቀጥሎ ፡ የአክሱምን ፡ ታሪክ ፡ ለመጻፍ ፡ ስንነሣ ፡ ከኖ ፡ ወገን ፡ ጽሑፍ ፡ ሲያጥርብን ፡ በግድ ፡ የጥንት ፡ የግሪክና ፡ የሮማ ፡ የግብፅ ፡ ጸሐፊዎችና ፡ መርማሪዎች ፡ እያዩም ፡ በሬም ፡ እየጻፉ ፡ ለዛሬ ፡ ጸሐፊ ፡ ትተው ፡ ወደ ፡ ፈረንሳዊና ፡ ወደ ፡ ኢጣሊያ ፡ ሉተር ጉሞ ፡ ሊነበብ ፡ ከቻለው ፡ ወደ ፡ መፈላለግ ፡ መሄድ ፡ ግዴታ ፡ ነው ። ።

ስለዚህ ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ የምናነበው ፡ በመጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ የኑብያ ፡ ታሪክ ፡ ከግብፅ ፡ ተያይዞ ፡ የአክሱሙ ፡ ከደቡብ ፡ ዓረብ ፡ ተዛምዶ ፡ ለአሁኑ ፡ መንግሥታችንም ፡ ለሥልጣኔውም ፡ ለፊደሉም ፡ ለቋንቋውም ፡ ለዘሩም ፡ ለልማዱም ፡ ሳባና ፡ ሀበሳት ፡ የመሰቡበት ፡ ይኸው ፡ ደቡብ ፡ ዓረብ ፡ መሆኑን ፡ በሰፊው ፡ እናያለን ። ለዛሬው ፡ ሥልጣኔያችንና ፡ ፊደላችን ፡ ቋንቋና ፡ ልማዳችን ፡ አባት ፡ ያልሆነውን ፡ የኑብያን ፡ ታሪክም ፡ በሰፊው ፡ ስንመለከት ፡ ከአክሱም ፡ ጋር ፡ የልዩነቱን ፡ ወይም ፡ የግንኙነቱን ፡ መጠን ፡ አንባቢ ፡ ራሱ ፡ እንዲገነዘበውና ፡ የራሱን ፡ ፍርድ ፡ እንዲሰጥ ፡ ጭምር ፡ ነውና ፡ እነሆ ፡ አሁን ፡ ስለኢትዮጵያና ፡ ስለግብፅ ፡ ቅድሚያ ፡ ስለነገደ ፡ ካም ፡ ስለነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ፣ ናምነውም ፡ ብንጠራጠረውም ፡ እስካሁን ፡ በየመጽሐፉ ፡ ስለሚገኙ ፡ የነገሥታት ፡ ዝርዝር ፡ ስለኑብያውና ፡ ስለአክሱም ፡ መንግሥት ፡ ልዩነትና ፡ ግንኙነት ፡ በየምዕራፉ ፡ እንመልከት ። ።

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

ባገራችን ፡ ጽሑፍ ፡ የሚገኘው ፡ የነገደ ፡ ካምና ፡ የነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ አመሠራረት — የነገሥታቱ ፡ የተለመደ ፡ ዝርዝር — በውጭ ፡ አገር ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገድና ፡ ልማድ ። ።

ባዕኛው ፡ ምዕራፍ ፡ እንደተመለከትነው ፡ የእስራኤልና ፡ የግሪክ ፡ ጸሐፊዎች ፡ እነሙሴ ፤ እነሐሜር ፡ እነሔሮዳቱስ ፡ ነቢያቱ ፡ እነኢሳይያስ ፡ ይህ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዘር ፡ በኩሽ ፡ የዘር ፡ ሐረግ ፡ መውረዱ ፡ ሲታወቃቸው ፡ እንደግብፃውያን ፡ የኩሽ ፡ አገር ፡ በኋላ ፡ መጥቶ ፡ በተደባለቀበት ፡ ምክንያት ፡ የሴም ፡ ዘርነቱ ፡ ሲሰማቸው ፡ የሳባ ፡ አገር ፡ ይሉታል ። ስለዚህ ፡ ከነሱ ፡ ወዲህ ፡ የተነሣው ፡ ጸሐፊ ፡ ሁሉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በሰፊው ፡ ግዛቱ ፡ የካምና ፡ የሴም ፡ ድብልቅ ፡ ዘር ፡ መሆኑን ፡ ተረድቶ ፡ በዚሁ ፡ ጽሑፉን ፡ ሲቀጥል ፡ ይኸን ፡ እያያዝ ፡ የቅርብ ፡ ዘመን ፡ ደንበኛ ፡ መርማሪዎች ፡ እነዮሴፍ ፡ ሐለቪ ፡ እነግላዳር ፡ እነከንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ አጽድቀውታል ። ።

ከኛም ፡ ወገን ፡ ታሪከ ፡ ነገሥታችን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ስለነገደ ፡ ካም ፡ (የኩሽ ፡ አባት) ፤ ስለነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ስለመደባለቁም ፡ ይጽፋል ። የሁለቱንም ፡ ነገድ ፡ የነገሥታት ፡ ስምና ፡ የነገሡበትን ፡ ዘመን ፡ ዘርዝሮ ፡ ይጽፋል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ እስካሁን ፡ እየተጻፈ ፡ የቆየውን ፡ ከመጻፍ ፡ በቀር ፡ ስለስማቸው ፡ ዝርዝር ፤ ስለቅደም ፡ ተከተላቸው ፡ ስለዘመኑ ፡ ትክክልነት ፡ ለማመንም ፡ ለመካድም ፡ የዘመኑ ፡ ርቀትና ፡ የማስረጃው ፡ ጥፋት ፡ አያስችለንም። ሐተታም ፡ ለመስጠት ፡ በመጠኑ ፡ ብንፈልግ ፡

የእነዚህ ፡ የነገሥታቱ ፡ ዝርዝር ፡ በኩብያ ፡ በናፓታና ፡ በመርዌ ፡ የነበሩት ፡ የኩሽ ፡ ዘር ፡ የሆኑት ፡ ነገሥታት ፡ በዓረብ ፡ አገርና ፡ ከዚያ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ኢትዮጵያ ፡ የተሻገሩት ፡ የሰባ ፡ ነገሥታት ፡ ተደባልቀው ፡ የተጻፉ ፡ ይመስላል ። ለምሳሌ ፡ የነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ዘር ፡ ከሚላቸው ፡ ነገሥታት ፡ ውስጥ ፡ ከንግሥተ ፡ ሳባ ፡ አምስተኛ ፡ የሆነውን ፡ አሜን ፡ ሐቴብ ፡ ይላል ። አሜን ፡ ሐቴብ ፡ አጠራሩ ፡ ግብፃዊ ፡ ያም ፡ ቢቀር ፡ የናፓታ ፡ የኩሽ ፡ እንጂ ፡ የሳባ ፡ አጠራር ፡ አይደለም ። በሺ፩ ፻፹፡ ዓመት፡ ከክርስቶስ፡ ልደት፡ በፊት ፡ አሜን ፡ ሐቴብ ፡ አንደኛ፡ የሚባል፡ የግብፅ ፡ ንጉሥ ፡ ነበር ። የዚህ ፡ ዓይነት ፡ አጠራር ፡ በስሕተት ፡ መድረሱ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ በሞግሽነት ፡ ተወስዶ ፡ እንደሆነ ፡ አናውቅም ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ከዘፍጥረት ፡ ምዕራፍ ፡ ፲ ፡ ወጥቶ ፡ የተዘጋጀው ፡ ከአዳም ፡ የወረደው ፡ የዘር ፡ ሐረግ ፡ እንደሚያሳየን ፡ መሠረቱ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስና ፡ ታሪክ ፡ ነገሥታችን ፡ ሆኖ ፡ ከዚያ ፡ ያገራችን ፡ ጸሐፊዎች ፡ ሁሉ ፡ አጭር ፡ መነሻ ፡ ጨምረው ፡ በየመጽሐፋቸው ፡ የሚዘረዝሩት ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

ለኖኅ ፡ ሴም ፡ ካም ፡ ያፌት ፡ የሚባሉ ፡ ፫ ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ፡ ከነዚሁ ፡ ካም ፡ ኩሳን ፡ (ኩሽን) ፡ ምሥራይን ፤ ፋጥን ፤ ከነዓንን ፡ ይወልዳል ። በፋንታው ፡ ኩሳ ፡ (ኩሽ) ፡ ሳባ ፡ ሐዊላ ፤ ሰጥታም ፤ ረዕማ ፤ ነምሩድ ፡ የሚባሉትን ፡ ፭ ፡ ልጆች ፡ ወለዶ ፡ የነርሱ ፡ ዘሮች ፡ በርክተው ፡ እስከ ፡ ኑብያ ፡ ድረስ ፡ ያላውን ፡ አገር ፡ አቅንተው ፡ ሲኖሩ ፡ ለነርሱም ፡ እስከ ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ መምጣት ፡ ድረስ ፡ ሽ፱ ፡ ነግሥታት ፡ ነበርዋቸው ፡ ይልና ፡ ስማቸውንና ፡ የነገሡበትን ፡ ዘመን ፡ እንደዚህ ፡ እያለ ፡ ያከታትላል ።

ተርታ	ስም	የግዛት ፡ ዘመን ፡	ዓመተ ፡ ዓለም ፡ ከክር ፡ ልደት ፡ በፊት ፡
፩	ሰጥታህ ፡ (ሳጢታ) ፡	፴	፱፻፭፻፺፭—፱፻፭፻፷፭
፪	ኤሌክትሮን ፡	፴፩	፱፻፭፻፷፭ — ፱፻፬፻፵፭
፫	ነቢር ፡	፴፩	፱፻፬፻፵፭—፱፻፬፻፱፭
፬	አሜን ፡ አንደኛ ፡	፭፩	፱፻፬፻፱፭ —፱፻፬፻፷፬
፭	ነሕሴት ፡ ናይስ ፡	፴፩	፱፻፬፻፷፬ – ፱፻፬፻፬
፮	ታርኪም ፡	፳፱	፱፻፬፻፬ –፱፻፫፻፭
፯	ሳባ ፡ ፭ኛ ፡	፴፩	፱፻፫፻፭–፱፻፫፻፺፭
፰	ሶፋሪድ ፡	፴፩	፱፻፫፻፺፭–፱፻፫፻፷፭
፱	እስክንዲ ፡	፳፭	፱፻፫፻፷፭ - ፱፻፱፻፺
፲	ሆህይ ፡ ስጥዎ ፡	፴፭	፱፻፱፻፺ –፱፻፱፻፷፭
፲፩	አህያፕ ፡	፳	፱፻፥፻፺፭ –፱፻፱፻፵፭
፲፪	አድጋስ ፡	፴፩	፱፻፱፻፵፭–፱፻፱፻፭

ተከታታይ	ስም ፡	የግዛት ፡ዘመን፡	ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡
፲፫	ባኩንዶን ፡ መሊስ ፡	፭፭	፱፻፱፻፭ –፱፻፭፻፶
፲፬	ማንቱራይ ፡ ሀቀቢ ፡	፴፭	፱፻፭፻፶ –፱፻፭፻፸፭
፲፭	ራክሁ ፡ ድድሜ ፡	፵	፱፻፭፻፸፭–፱፻፭፻፲፭
፲፮	ሶቢ ፡ አንደኛ ፡	፵	፱፻፭፻፲፭ –፱፻፶፭
፲፯	አዜጋን ፡ ፊርያን ፡	፵	፱፻፶፫ –፱፻፱፭
፲፰	ሱስሑል ፡ አቶዛኔስ	፭	፱፻፱፭ –፱፻፴፭
፲፱	አሚን ፡ ሁለተኛ ፡ ጸዊዛ ፡	፲፭	፱፻፴፭ –፱፻፭
፳	ራሚንጳህቲ ፡ መስልኔ ፡	፭	፱፻፭ –፱፻
፳፩	ዋኑና ፡	፫ ቀን	
፳፪	ጲያሪ ፡ አንደኛ ፡	፲፭	፱፻ –፭፻፱፻፶፭

ሁል ፡ ጊዜ ፡ እንደአገራችን ፡ የተለመደ ፡ አጻጻፍ ፡ እነዚህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጻፉት ፡ ነገደ ፡ ካም ፡ የተባሉት ፡ ነገሥታት ፡ ናቸው ። እንደዚሁም ፡ የካም ፡ ወንድም ፡ ሴም ፡ ፱ ፡ ልጆች ፡ ይወልዳል ። ከ፱ኙ ፡ አንዱ ፡ አርፋክስድ ፡ ነው ። እርሱም ፡ ሳላህን ፡ ሳላህ ፡ ኤቦርን ፡ ፋሌቅንና ፡ ዮቅጣንን ፡ ይወልዳል ። ዮቅጣን ፡ ደግሞ ፡ ፲፫ ፡ ልጆች ፡ ይወልዳል ፡ ከነዚሁ ፡ ጅቱ ፡ ሳባ ፡ አባል ፡ አፊር ፡ አቢማር ፡ ሐዊላ ፡ ከወንድሞቻቸው ፡ ተለይተው ፡ የመካከል ፡ ምሥራቅን ፡ አገር ፡ ትተው ፡ ወደየመን ፡ መጥተው ፡ ተቀመጡ ። በየመንም ፡ ሳሉ ፡ የሕንድ ፡ ነገሥታት ፡ እየ ወጉ ፡ ቢያስቸግርዋቸው ፡ እላይ ፡ የተጻፈው ፡ እንደሚያመለክተው ፡ የካሙ ፡ ዘር ፡ ጲያሪ ፡ በነገሠበት ፡ ዘመን ፡ ፩ሺ፱፻፶ ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ የመንን ፡ ለቀው ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተሻግረው ፡ መጡና ፡ ሦስቱ ፡ ነገዶች ፡ ሳባ ፡ በትግሬ ፡ አባል ፡ በአዳል ፡ አፊር ፡ በውጋዴን ፡ ተቀመጡ ። እንደመጡም ፡ መጦመሪያውን ፡ ጅቱን ፡ ዓመት ፡ ለካሙ ፡ ነገድ ፡ ንጉሥ ፡ ለጲያሪ ፡ ገብረዋል ።

በዚህ ፡ መካከል ፡ የሕንድ ፡ ንጉሥ ፡ ራማ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መጥቶ ፡ ጲአሪን ፡ ወግቶ ፡ አሸንፎ ፡ መንግሥቱን ፡ ቀማው ። ሕዝቡንም ፡ እንደባሪያ ፡ ይገዛው ፡ ዠመር ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ እነዚህ ፡ ሦስቱ ፡ የዮቅጣን ፡ ልጆች ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ከያሉበት ፡ ተሰብስበው ፡ ራማን ፡ ወግተው ፡ ሠራዊቱን ፡ አሸንፈው ፡ እርሱንም ፡ ገደሉና ፡ ሕዝቡን ከባርነት ፡ ነፃ ፡ አወጡት ። በዚህም ፡ እነዚሁ ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ነገደ ፡ አግዓዝያን ፡ (ነፃ ፡ አውጭዎች ፡) የሚባል ፡ ስም ፡ ወጣላቸው ፡ ይላል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ የመንግሥቱ ፡ መሪነት ፡ ወደ ፡ ነገደ ፡ ካም ፡ ሳይመለስ ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ተዋግተው ፡ ያዳኑትን ፡ አገር ፡ ለራሳቸው ፡ ያዙት ፡ ማለት ፡ ነው ። ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ በነገደ ፡ ካም ፡ ተተክተው ፡ ኢትዮጵያን ፡ ማስተዳደራቸውን ፡ ይገልጽና ፡ በታሪክ ፡ ነገሥታችን ፡ እርሱንም ፡ መሠረት ፡ አድርገው ፡ በጻፉት ፡ በነዣን ፡ ሞሪዬ ፡ በነብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኅሩይ ፡ መጽሐፍ ፡ የነገሥታቱ ፡ ዝርዝራቸው ፡ እንደዚህ ፡ እያለ ፡ ይቀጥላል ።

ተከታታይ	ስም ፡	የግዛት፡ዘመን፡	ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡
፩	አክናሁስ፡ሳባ ፡ ፪ኛ ፡	፵፭	፩ሺ፱፻፹፭–፩ሺ፱፻፴
፪	ነክህቲ ፡ ካልንሶ ፡	፵	፩ሺ፱፻፴ –፩ሺ፰፻፺
፫	ከሲዮፒ ፡	፲፱	፩ሺ፰፻፺ –፩ሺ፰፻፷፩
፬	ሳቢ ፡ ፪ኛ ፡	፲፭	፩ሺ፰፻፷፩–፩ሺ፰፻፵፯
፭	ኢትዮጲስ ፡ ፩ኛ ፡	፵፯	፩ሺ፰፻፵፯ -፩ሺ፰፻፲
፮	ላከንዱን ፡ ሞወር ፡ አሪ ፡	፴	፩ሺ፰፻፲ -፩ሺ፯፻፷
፯	ቱትኤምሔብ ፡	፳	፩ሺ፯፻፷ –፩ሺ፯፻፵
፰	ሔርሐቶር ፡	፳	፩ሺ፯፻፵ –፩ሺ፯፻፴
፱	ኢትዮጲስ ፡ ፪ኛ ፡	፴	፩ሺ፯፻፴ –፩ሺ፯፻
፲	ሰኑካ ፡ ፪ኛ ፡	፲፯	፩ሺ፯፻ -፩ሺ፮፻፹
፲፩	በኑ ፡ ፩ኛ ፡	፰	፩ሺ፮፻፹-፩ሺ፮፻፷
፲፪	መ·ማዜስ ፡	፬	፩ሺ፮፻፷–፩ሺ፮፻፵
፲፫	አሩአሳ ፡	፯ ወር	
፲፬	አሚን ፡ አሶር	፴	፩ሺ፮፻፵፬ -፩ሺ፮፻፲፬
፲፭	አሪ ፡ ፪ኛ ፡	፴	፩ሺ፮፻፲፬ –፩ሺ፮፻፰
፲፮	ጲአሪ ፡ ፪ኛ ፡	፲፭	፩ሺ፮፻፰ –፩ሺ፮፻፺፯
፲፯	አሚንኤምሐት ፡ ፩ኛ ፡	፵	፩ሺ፮፻፺፯ –፩ሺ፮፻፶፯
፲፰	ፃውዕ ፡	፲፭	፩ሺ፮፻፶፯ –፩ሺ፮፻፸፪
፲፱	አክቲሳኒስ ፡	፲	፩ሺ፮፻፸፪ –፩ሺ፮፻፹፪
፳	ማንዲስ ፡	፲፯	፩ሺ፮፻፹፪ –፩ሺ፮፻፺፱
፳፩	ጵሮቶውስ ፡	፴፫	፩ሺ፮፻፺፱ –፩ሺ፯፻፳፩
፳፪	አሞይ ፡	፳፩	፩ሺ፯፻፳፩–፩ሺ፯፻፵
፳፫	ከንሲ ፡	፭	፩ሺ፯፻፵ –፩ሺ፯፻፺፭
፳፬	በኑ ፡ ፪ኛ ፡	፪	፩ሺ፯፻፺፭ -፩ሺ፯፻፺፯
፳፭	ሳቢ ፡ ፫ኛ ፡	፲፭	፩ሺ፯፻፺፯ –፩ሺ፰፻፴፫
፳፮	ጅጎንሶ ፡	፳	፩ሺ፰፻፴፫ -፩ሺ፰፻፶፫
፳፯	ሰኑካ ፡ ፫ኛ ፡	፲	፩ሺ፰፻፶፫ –፩ሺ፰፻፷፫
፳፰	አንጋበስ ፡ ፩ኛ ፡	፱	፩ሺ፰፻፷፫ –፩ሺ፰፻፺፰
፳፱	ሚአሙር ፡	፪ ቀን	
፴	ከለና ፡	፲፩	፩ሺ፰፻፺፰ –፩ሺ፱፻፱
፴፩	ዘግዱር ፡	፱	፩ሺ፱፻፱ –፲ሺ፱፻፯
፴፪	ሔርሐቶር ፡ ፪ኛ ፡	፴	፩ሺ፱፻፯ –፩ሺ፱፻፷፯
፴፫	ሔርሐቶር ፡ ፫ኛ ፡	፩	፩ሺ፱፻፷፯ –፩ሺ፱፻፷፰
፴፬	ኔክቱ ፡ ፩ኛ ፡	፳	፩ሺ፱፻፷፰ -፩ሺ፱፻፹፯
፴፭	ቲቶን ፡ ሶትዮ ፡	፲	፩ሺ፱፻፹፯ –፩ሺ፱፻፺፯

ተከታታይ	ስም ፡	የግዛት፡ዘ መን፡	ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡
፴፩	ሔርመንቱ ፡ ፩ኛ ፡	፩ ወር	
፴፪	አሜን ፡ ኤምሐት ፡ ፪ኛ	፭	፩፻፪፻፸፯-፩፻፪፻፸፩
፴፫	ከንሳብ ፡ ፩ኛ ፡	፭	፩፻፪፻፸፩-፩፻፪፻፷፯
፴፬	ከንሳብ ፡ ፪ኛ ፡	፭	፩፻፪፻፷፯- ፩፻፪፻፷፩
፴፭	ሰኑካ ፡ ፩ኛ ፡	፭	፩፻፪፻፷፩-፩፻፪፻፭፯
፴፮	አንጋቦ ፡ ፪ኛ ፡ ሕዝባይ ፡	፴	፩፻፪፻፭፯-፩፻፩፻፶፯
፴፯	አሜን ፡ አስታት ፡	፴፩	፩፻፩፻፶፯- ፩፻፩፻፱፯
፴፰	ሔርሔር ፡	፲፯	፩፻፩፻፱፯ ፩፻፩፻፴
፴፱	ፒያንኪያ ፡ ፩ኛ	፱	፩፻፩፻፴—፩፻፩፻፴፩
፵፩	ጥኖትሲም ፡ ፩ኛ ፡	፲፯	፩፻፩፻፴፩-፩፻፩፻፲፩
፵፪	ጥኖትሲም ፡ ፪ኛ ፡	፴፩	፩፻፩፻፲፩-፩፻፫፲
፵፫	ማሳሔርታ ፡	፲፯	፩፻፫፲—፩፻፱፯
፵፬	ራሜንከፐርም ፡	፲፩	፩፻፱፯—፩፻፵፫
፵፭	ጥኖትሴም ፡ ፫ኛ ፡	፯	፩፻፵፫ -፩፻፴፯
፵፮	ሳቢ ፡ ፩ኛ ፡	፲	፩፻፴፯ -፩፻፳፯
፵፯	ተዋስያ ፡ ዩውስ ፡	፲፫	፩፻፳፯ -፩፻፲፫
፵፰	ማክዳ ፡ ንግሥት ፡	፴፩	፩፻፲፫ -፱፻፹፰

እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ነገሥታት ፡ የምንላቸው ፡ አብዛኞቹ ፡ ክቡር ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ሳሩይ ፡ በዋዜማ ፡ መጽሐፋቸው ፡ እንዳሉት ፡ እንደባላባት ፡ በውስጣቸው ፡ ያለውን ፡ ነገድ ፡ ያስተዳድሩት ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ደንቡ ፡ ዘውድ ፡ ደፍተው ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሥ ፡ ተደርጎላቸው ፡ በንጉሥነት ፡ ስም ፡ የገዙ ፡ አይመስልም ። በዚያን ፡ ዘመን ፡ የዚህ ፡ ዕድል ፡ የገጠማቸው ፡ መንግሥቶች ፡ የግብፅ ፡ መንግሥትና ፡ ሐሙራቢ ፡ የመሠረተው ፡ የባቢሎን ፡ ከዚያም ፡ የቻይናና ፡ የሕንድ ፡ መንግሥታት ፡ ናቸው ። የነዚህ መንግሥታት ፡ ሥልጣኔ ፡ ቀዳሚነት ፡ የታወቀው ፡ ሊቃውንት ፡ የነበሩበትን ፡ ከተማ ፡ እያስቆፈሩ ፡ ልዩ ፡ ያማልክትና ፡ የነገሥታት ፡ ሐውልት ፡ እያገኙ ፡ በሐውልቱ ፡ የተቀረጸውን ፡ ጽሑፍ ፡ በጥልቅ ፡ ምርመራ ፡ እየተረጐሙ ፡ በሰጡት ፡ ማስረጃ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ወደፊት ፡ በአክሱም ፡ ታሪክ ፡ ላይ ፡ እንደምናገኘው ፡ ማክዳ ፡ ንግሥት ፡ ከአርቄና ፡ ከአንጋቦ ፡ ተከታትላ ፡ መምጣቷን ፡ ታሪክ ፡ ነገሥታችን ፡ ስለሚገልጽና ፡ ይኸ ፡ ያሁኑ ፡ ሴላ ፡ ዓይነት ፡ ዝርዝር ፡ ስለሚሰጥ ፡ በዝርዝሩ ፡ ሙሉ ፡ እምነት ፡ መስጠት ፡ ችግር ፡ ነው ።

ምናልባት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጥንታዊ ፡ ከተማ ፡ እየተቆፈረ ፡ የተደበቀ ፡ ሐውልት ፡ ተገኝቶ ወደ ፡ ብርሃን ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፡ እንደዚሁ ፡ እንዳለ ፡ አንብበን ፡ እንለፍና ፡ የዚህኑ ፡ የጥንት ፡ ሕዝብ ፡ ኑሮ ፡ እንመልከት ።

የቀድሞ ፡ ሕዝባችን ፡ ኑሮ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ እንደነበረ ፡ በዝርዝር ፡ የሚ
ገልጽ ፡ ጽሑፍ ፡ አይገኝም ። አጭር ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ታሪክ ፡ የሚባለው ፡
የአለቃ ፡ ታዬ ፡ መጽሐፍም ፡ በሰፊው ፡ አይገልጽም ። ቢሆንም ፡ ከክርስቶስ ፡
ልደት ፡ በፊት ፡ ከሦስት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ወዲያ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በምንም ፡
ዓይነት ፡ ቢሆን ፡ ሥልጣኔ ፡ የነበረውና ፡ የኑሮው ፡ ደረጃ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አይመ
ስልም ። ስለዚህም ፡ የሚናገር ፡ ጽሑፍ ፡ ከኛ ፡ ወገን ፡ የለንም ።

ስለዚህ ፡ ከራሳችን ፡ ስናጣ ፡ የነዚህ ፡ የነዋሪዎቹ ፡ የነገደ ፡ ካምና ፡ ከምሥ
ራቅ ፡ የመጡት ፡ የነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ሕዝቦች ፡ እንዴት ፡ ይኖሩ ፡ እንደነበረ ፡
ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ጽሑፍ ፡ ሄደን ፡ የሚያከራውንም ፡ የሚያስቀይመውንም ፡
እየፈለግን ፡ መመልከት ፡ አለብን ። የሚያከራው ፡ በ፱ነኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡
የነበረው ፡ ሆሜርና ፡ይልቁንም ፡በ፯ኛው ፡መቶ ፡ዓመት ፡የነበረው ፡ሄሮዱት ፡የጻፉት ፡ነው ።
እነሱም ፡ ከብዙዎቹ ፡ ንግግሮቻቸው ፡ ውስጥ ፡ እንደዚህ ፡ ይላሉ ። ኢትዮጵያው
ያን ፡ ታላላቆች ፡ መልካቸው ፡ ያማረ ፡ የሰውነታቸው ፡ ቅርጽ ፡ ደንበኛ ፡ የሆነ ፡
ጸድቆች ፡ በጎ ፡ አድራጊዎች ፡ ለሥራ ፡ የማይደክሙ ፡ ጥበበኞች ፡ በሩቅ ፡ ሥፍራ
የሚኖሩ ፡ አማልክት ፡ የሚወዷቸው ፡ በንደበታቸው ፡ ሐሰት ፡ የማይገባ ፡ በጦ
ርነትና ፡ በርጅና ፡ ካልሆነ ፡ በስተቀር ፡ በበሽታ ፡ የማይሞቱ ፡ ናቸው ።

በተረፈ ፡ በመገለመሪያው ፡ ምዕራፍ ፡ እንዳልነው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ስም ፡
ነቢያቱ ፡ እነኢሳይያስ ፡ እነሶፎንያ ፡ ወደዝርዝር ፡ ጉዳይ ፡ ሳይገቡ ፡ በትንቢታ
ቸው ፡ ውስጥ ፡ እንደአጋጣሚ ፡ እየጠቀሱት ፡ አልፈዋል ። በነሱም ፡ ጽሑፍ ፡
ውስጥ ፡ ስም ፡ ማውሳት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ስለኢትዮጵያውያን ፡ ኑኖ ፡ የሚና
ገር ፡ዝርዝር ፡ ጽሑፍ ፡ አይገኝም ።

ስለዚህ ፡ ከሁሉ ፡ ይበልጥ ፡ ከኖብያ ፡ እስከ ፡ ኤርትራ ፡ ባሕር ፡ ድረስ ፡
በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ተበታትኖ ፡ ስለሚኖረው ፡ ሕዝባችን ፡ በሰፊው ፡ የጻፉ ፡ ከዚህ
ቀደም ፡ በምዕራፍ ፡ ፪ ፡ የጠቀስናቸው ፡ አጋታርሺድ ፡ ኤራቶስቴን ፡ ዲዮዶር ፡
የሚባሉ ፡ የግሪክ ፡ ተወላጆች ፡ ናቸው ። ኤራቶስቴን ፡ በ፫ተኛው ፡ መቶ ፡
ዓመት ፡ አጋታርሺድ ፡ በ፪ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ላይ ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ የነ
በሩ ፡ ናቸው ። አጋታርሺድ ፡ የበጥሊሞስ ፡ ሰባተኛ ፡ (የግብጽ ፡ ንጉሥ ፡)መምህር ፡ የነ
በረ ፡ ነው ። እሱም ፡ በዘመኑ ፡ የታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ ጽፎ ፡ የቀረው ፡ ሁሉ ፡
ጠፍቶ ፡ MARE ERYTHREO የኤርትራ ፡ ባሕር ፡ የሚባለው ፡ መጽሐፉ ፡
ብቻ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ይገኛል ። የሱንም ፡ መጽሐፍ ፡ መሠረት ፡ እያደረጉ ፡ ዣን ፡
ሞሪዬ ፡ JEAN MORIE HISTOIRE d' ETHIOPIE በሚባለው ፡ መጽሐፉ ፡ ፡
ባንደኛው ፡ ቮልዩም ፡ በምዕራፍ ፡ ሁለት ፡ ገጽ ፡ ፮፩–፱፪ ፡ ኮንቲ ሮሲኒ ፡ Conti Rossini
STORIA d' ETIOPIA በሚባለው ፡ መጽሐፉ ፡ በምዕራፍ ፡ ሁለት ፡ ከገጽ ፡ ፶፯ ፡
፷፫ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ተበታትኖ ፡ የሚኖረውን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገድ ፡ ጠቅሰውት ፡
ይገኛል ። ቃሉም ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተጻፈው ፡ ነው ።

፩ኛ ፡ አባ ፡ ታሊት ፡ ወይም ፡ ስትሩቲአፋሹ ፡ ትርጓሜውም ፡ ስሆን ፡ የም ትባለዋን ፡ እንስሳ ፡ የሚበሉ ፡ ግማሾቹ ፡ አዕዋፍ ፡ የሚበሉ ፡ ዓባይ ፡ ምንጭ ፡ አጠገብ ፡ የሚኖሩ ፡ ልብሳቸውም ፡ ሥጋዋን ፡ የሚበሉት ፡ የስሆን ፡ ቆዳ ።

፪ኛ ፡ አዳሊት ፡ የሚባሉት ፡ ከግብፅ ፡ ጠፍተው ፡ መጥተው ፡ የአዳሊስን ፡ ቅጽር ፡ ምሽግ ፡ ሠርተው ፡ ግማሾቹ ፡ በዋሻ ፡ የሚኖሩ ።

፫ኛ ፡ አአጐሴፋል ፡ ራሳቸው ፡ ጥንዚዛ ፡ የሚመስል ፡ ጥንዚዛ ፡ የሚበሉም

፬ኛ ፡ አኤጐሊዬሴፋል ፡ ኔት ፡ ለምትባለው ፡ ሴት ፡ ጣዖት ፡ የሚሰግዱ ።

፭ኛ ፡ አክሪሎፋሹ ፡ አንበጣን ፡ የሚበሉ ፡ ቁመታቸው ፡ አጫጭር ፡ ሰው ነታቸው ፡ ቀጭን ፡ በጣም ፡ የሚሮጡ ፡ ዕድሜያቸው ፡ ከሠላሳ ፡ ዓመት ፡ የማይ በልጥ ፡ ይኸውም ፡ ማለት ፡ በቁምጥና ፡ በሽታ ፡ እያለቁ ፡ በቶሎ ፡ የሚሞቱ ።

፮ኛ ፡ አሮቴር ፡ የሚባሉ ፡ ከአዳሊስ ፡ በሰሜን ፡ የሚኖሩ ።

፯ኛ ፡ አርታባቁት ፡ የሚባሉ ፡ በጫካ ፡ የሚኖሩ ።

፰ኛ ፡ አሳክያን ፡ ኤሴፋንቶፋሹ ፡ ዝሆን ፡ እያደኑ ፡ የሚበሉ ፡ ስማቸው ፡ አስማክ ፡ ማስሁአሽ ፡ የሚባሉ ፡ በዛሬው ፡ ሐማሴንና ፡ ሠናሂት ፡ የሚቀመጡ ፡ በቀን ፡ ዝሆንና ፡ ሌላም ፡ አውሬ ፡ ሲያድኑ ፡ እየዋሉ ፡ አዳራቸውን ፡ በዛፍ ፡ ላይ ፡ የሚያደርጉ ፡ የነብር ፡ ቆዳ ፡ የሚለብሱ ፡ ናቸው ። በነርሱ ፡ ዘንድ ፡ ሴትና ልጅ ፡ የጋራ ፡ ነው ። ከመከከላቸው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በጣም ፡ ሽምግሎ ፡ የማይ ሞት ፡ ሲሆን ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ አንዲሞት ፡ ይጠይቁታል ፡ እምቢ ፡ ያለ ፡ እንደሆነ ፡ እንደልማዳቸው ፡ አሮጊውን ፡ ሰው ፡ ከከርማ ፡ በሬ ፡ ጭራ ፡ ጋር ፡ አሥረው ፡ እያስጐተቱ ፡ ይገሉታል ።

፱ኛ ፡ አባሊት ፡ ከባብ ፡ ኤል ፡ ማንጄብ ፡ ባሕር ፡ ጅምሮ ፡ ከርቤና ፡ ብርጉድ ፡ በብዙ ፡ በሚገኝበት ፡ በዛሬው ፡ የአዳልና ፡ የሱማሌ ፡ አገር ፡ የሚኖሩ ፡ (እነዚህም ፡ ከጀቹ ፡ ከየቅጣን ፡ ልጆች ፡ ያንዱ ፡ የአበል ፡ ዘሮች ፡ መሆናቸው ፡ ነው ።)

፲ኛ ፡ አክሱማውያን ፡ በዛሬው ፡ አክሱም ፡ አጠገብ ፡ የሚኖሩ ።

፲፩ኛ ፡ ባርጂን ፡ የሚባሉ ፡ በዛሬው ፡ ባርክ ፡ በሚባለው ፡ አውራጃ ፡ በዋሻ ፡ የሚኖሩ ።

፲፪ኛ ፡ ብሌሚ ፡ (ብሌማ ፡) የሚባሉ ፡ ከአትባራ ፡ (አስታበራስ)፡ ወንዝ ፡ በሰሜን ፡ እስከ ፡ ላሰላይ ፡ ግብፅ ፡ ድረስ ፡ የሚቀመጡ ፡ ዘራቸው ፡ ከክነዓን ፡ ልጅ ፡ ከኼት ፡ ወይም ፡ ከኬት ፡ የወረዱ ፡ የዛሬ ፡ ዘመን ፡ ጸሐፊዎች ፡ የበኋ ፡ ዘር ፡ የሚሉዋቸው ፡ ናቸው ። እነሱም ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ አብዛኞቹ ፡ በዋሻ ፡ የሚቀመጡ ፡ ቢሆኑ ፡ ሠላሳ ፡ የሚሆኑ ፡ ሬጂል ፡ ስለነበራቸውና ፡ በራሳቸው ፡ ቋንቋ ፡ የሚናገሩ ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ በዚያው ፡ በመጠኑ ፡ ሥልጡኖች ፡ መሆናቸውን ፡ ያስረዳል ። እነሱም ፡ በቀይ ፡ ድርጭት ፡ ያመልኩ ፡ ነበር ። ኑሮአቸው ፡ እየተራረፈ ፡ ሥር ፡ በብዙ ፡ በታ ፡ ራሳቸው ፡ በሠሩት ፡ በዋሻ ፡ ከተማ ፡ ይቀመጡ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ በጠባዩ ፡ ዋሽነት ፡

ያለውን ፡ ብቻ ፡ አይመርጡም ፡ ነበር ። እነሱም ፡ ላንድ ፡ ጊዜ ፡ ጦርነት ፡ ግፊ ፡ ሺህ ፡ ወታደር ፡ ፱፻ ፡ መንኰራኩር ፡ ያቀርቡ ፡ ነበር ፡ ይባላል ።

፲፫ኛ ፤ ሲናሞልሽ ፡ የሚባሉ ፡ ጭንቅላታቸው ፡ የውሻ ፡ የሚመስል ፡ የውሻ ፡ ወተት ፡ የሚጠጡ ፡ ተኩላ ፡ የሚበሉ ፡ መልክቸው ፡ ጥቁር ፡ ፉንጋ ፡ ረጃጅሞች ፡ ጫማቸው ፡ ትልልቅ ፡ ማናቸውንም ፡ አውሬ ፤ አድነው ፡ ሥጋውን ፡ በልተው ፡ ቆዳውን ፡ አለስልሰው ፡ የሚለብሱ ፡ ናቸው ። እነዚህም ፡ አውሬና ፡ ጎሽ ፡ ለማደን ፡ እንዲያግዛቸው ፡ እንደከብት ፡ የውሻ ፡ መንጋ ፡ ያረቡ ፡ ነበር ።

የነሱ ፡ አማልክቶቻቸው ፡ ነገሥታቶቻቸው ፡ ነበሩ ። ነገሥታቱም ፡ ተግልጠው ፡ በመታየት ፡ ምክንያት ፡ እንዳይናቁ ፡ ዘወትር ፡ በሕዝብ ፡ መክበል ፡ ተሸፍነው ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። እነዚህ ፡ ዘሮች ፡ ዛሬ ቍናማ ፡ እየተባሉ ፡ የሚጠሩ ፡ ናቸው ።

፲፬ኛ ፤ ሲኔሽ ፡ በድርቅ ፡ አገር ፡ የሚኖሩ ፡ በረጅም ፡ አንከሴ ፡ በፍላጻ ፡ በድን ጋይ ፡ አውሬ ፡ እያደኑ ፡ የሚኖሩ ፡ ቍጥራቸው ፡ ያነሰ ።

፲፭ኛ ፤ ዳሬማስ ፡ በዋሻ ፡ የሚኖሩ ።

፲፮ኛ ፤ ደማዛን ፡ በዛሬው ፡ ደምበሻን ፡ በዋሻ ፡ የሚኖሩ ።

፲፯ኛ ፡ ኤላፎሴፋል ፡ ጭንቅላታቸው ፡ ዘንዶ ፡ ወይም ፡ ድኩላ ፤ ጢንዝዛ ፡ የሚመስል ፡ ሴት ፡ በሚባል ፤ ረሻም ፡ ዋልያ-አሰማ-አህያ ? ጣያት ፡ የሚያመልኩ ።

፲፰ኛ ፤ ጋሊ ፡ ጋላ ? በዋሻ ፡ የሚኖሩ ፡ በጥሊሞስ ፡ ሬላደልፍ ፡ ፀያፀጅ-ፀያፀሟ ፡ ሜዐሞት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ያስገበራቸው ።

፲፱ኛ ፤ ሐርፒ ፡ ወይም ፡ ሒዬራክሴፋል ፡ ጭንቅላታቸው ፡ የአሞራ ፡ ጭንቅላት ፡ የሚመስል ፡ በዓባይ ፡ ዳር ፡ የሚኖሩ ፡ እነዚህም ፡ የግሪክ ፡ የተረት ፡ መጽሐፍ ፡ እንደሚለው ፡ ከበለዐታቸው ፡ ተጣልተው ፡ ከነልጆታቸው ፡ ከግሪክ ፡ አገር ፡ የመጡ ፡ የአምስት ፡ ልዑላት ፡ የግሪክ ፡ ሴቶች ፡ ገዢያምች ፡ ናቸው ። አገራቸውን ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ አንበጣ ፡ ስለሚያጠቃው ፡ በረኃብ ፡ ምክንያት ፡ ጐረቤቶቻቸውን ፡ በዘረፋ ፡ የሚያስፈሩ ከልጆቻቸው ፡ ውስጥ ፡ ለጣያት ፡ እየአረዱ ፡ የሚሰዉ ፡ ናቸው ።

፳ኛ ፤ ሔሊንስ ፡ በዛሬው ፡ በሕር ፡ ኤል ፡ ጋዛል ፡ በሚባለው ፡ ረግረግ ፡ በታ ፡ የሚኖሩ ።

፳፩ኛ ፤ ሔማንቶፖድ ፤ ቅልጥማቸው ፡ ደረቅ ፡ በፉጫ ፡ ዛፍና ፡ ተራራ ፡ በመውጣት ፡ ማንም ፡ የማይቀድማቸው ።

፳፪ኛ ፤ ሒፖሽ ፡ ፈረሰኞች ፡ ምግባቸውም ፡ የፈረስ ፡ ሥጋ ፤ ልብስ ፡ በደንብ ፡ የሚለብሱ ፤ ጠጉራቸውን ፡ የሚሰሩ ፤ መልክቸው ፡ ያማረ ፤ ቍመታቸው ፡ የረዘመ ፡ ከግብያች ፡ ጋር ፡ በጦርነትም ፡ በንግድም ፡ ስለሚገናኙ ፡ አምልክአቸውም ፡ እንደ ፡ ግብያች ፡ አሲሪስና ፡ ኑም ፡ በሚባሉ ፡ ጣያቶች ፡ ነበር ።

ፀቨኛ ፤ ሂፖፖታሞሴፋል ፡ ጭንቅላታቸው ፡ ጉማሬ ፡ የመሰሉ ።

ፀፀኛ ፤ ሐሎፋኝ ፡ የዛፍ ፡ ሥርና ፡ የዛፍ ፡ ቀምበጥ ፡ የሚመገቡ ፡ ከተማቸው ፡ ኬብሐ ፡ የሚባል ። በነሱ ፡ ዘንድ ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ የነገድ ፡ እልቅና ፡ የሴት ፡ ነው ። የመንገሥት ፡ መብት ፡ ያላት ፡ ሴት ፡ ነች ። ሕዝቦቹ ፡ ሰውነታቸው ፡ ቀጭን ፡ ቀል ጣፋ ፡ ራቁታቸውን ፤ የሚሄዱ ፡ ኑት ፡ በሚባል ፡ ወርክ ፡ አድባር ፡ የሚያመልኩ ፡ ናቸው ፡ በነሱ ፡ ዘንድ ፡ ሴት ፡ የጋራ ፡ ነው ፡ ይኸውም ፡ ማለት ፡ የግል ፡ የባልና ፡ ሚስት ፡ ጋብቻና ፡ ኑሮ ፡ ሳይሆን ፡ ተደባልቆ ፡ በማሕበር ፡ መኖር ፡ ማለት ፡ ነው ።

ፀፎኛ ፤ ሐኢሴፋል ፡ ጭንቅላታቸው ፡ ጥንዚዛ ፡ የሚመስል ። በሴት ፡ (ፀሐይ) ፡ የሚያመልኩ ፡

ፀፏኛ ፤ ኤቢዮሴፋል ፡ ጭንቅላታቸው ፡ አሞራ ፡ የሚመስል ።

ፀፐኛ ፤ ቄድሮሴያን ፡ ወይም ፡ አክቲዮፋኝ ፡ ዓሣ ፡ የሚመገቡ ፡ በቀይ ፡ ባሕር ፡ ዳር ፡ የሚኖሩ ፡ ጭንቅላታቸው ፡ የዓሣ ፡ የሚመስል ፡ ራቁታቸውን ፡ የሚ ሄዱ ፡ የጦር ፡ መሣሪያቸው ፡ ሰይፋማ ፡ ድንጋይና ፡ የፍየል ፡ ቀንድ ። በነሱ ፡ ዘንድ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ የክብት ፡ መንጋ ፡ የጋራ ፡ ነው ፡ በመካከላቸው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ማሕበራዊ ፡ ኑሮ ሴኖር ፡ ከጎረቤቶቻቸው ፡ ጋር ፡ በንግድም ፡ በጋብቻም ፡ አይገናኙም ፡ ነበር ። ምግባ ቸው ፡ ዓሣ ፡ ስለነበረ ፡ አብዛኛ ፡ ጊዜ ፡ እርጥቡን ፡ እየበሉ ፡ የቀረውን ፡ በፀሐይ ፡ እያደረቁ ፡ ለክርሞ ፡ ያከማቻሉ ። ዓሣን ፡ በብዙ ፡ የሚይዝ ፡ እንደመረብ ፡ ያለ ፡ ብዙ ፡ መሣሪያና ፡ ብልሃት ፡ ነበራቸው ። ሬሳቸውንም ፡ በሕር ፡ በሞላ ፡ ወይም ፡ ሞገድ ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ጥልቁ ፡ ባሕር ፡ መስዶ ፡ እንዲጥለው ፡ እዳሩ ፡ በሚገኝ ፡ ድንጋይ ፡ ላይ ፡ ያስቀምጡታል ። በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ውጊያቸው ፡ አደገኛ ፡ ነው ። እነሱም ፡ እያባረሩ ፡ ከሚገሉ ፡ እየሸሹ ፡ በውርወራ ፡ የሚገሉት ፡ ይበልጣል ።

ፀፒኛ ፤ ከሊብ ፡ በዋሻ ፡ ከሚኖሩት ፡ አንደኛው ፡ ክፍል ።

ፀፑኛ ፤ ኬሎኖፋኝ ፡ ኤሊን ፡ የሚመገቡ ፡ ከባሕር ፡ የሚወጣ ፡ ዓሣና ፡ ሌላም ፡ እሙሬ ፡ እየበሉ ፡ በቅራፊውና ፡ በኤሊ ፡ ቆዳ ፡ ጅልባ ፡ እየሠሩ ፡ የሚሄዱ ፡ መኖሪያ ፡ ቤታቸውንም ፡ በዚሁ ፡ የሚከድኑ ፡ ናቸው ።

ፀፐኛ ፤ ክሬዮፋኝ ፡ እርጥብ ፡ ሥጋ ፡ የሚመገቡ ፡ በስናር ፡ ደቡብ ፡ የሚኖሩ ።

ፀፗኛ ። ላጉሴፋል ፡ መልካቸው ፡ የሚዳቋ ፡ ጭንቅላት ፡ የሚመስል ።

ፀፘኛ ፡ ማክሮቢያን ፡ ረጅም ፡ ዘመን ፡ የሚኖሩ ፡ የመርዌ ፡ ነገዶች ፤ ዕድልና ድድቅ ፡ ያላቸው ፡ አትክልትና ፡ ውሃ ፡ ጥብስ ፡ ሥጋ ፡ የሚመገቡ ፡ ዘፈን ፤ ጭፋሮ ንድሕና ፡ (እጥበት) ፡ የሚወዱ ፤ ቁጥራቸው ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ሚሊዮን ፡ የሚደርስ ፡ እገራቸው ፡ አሎ ፡ ወይም ፡ ሄለዎትራፔዝ ፡ (የፀሐይ ፡ አገር ፡) በሚባለው ፡ የዛሬው የሱናርና ፡ የሱዳን ፡ ግዛት ፡ ነው ። ከተማቸው ፡ መርዌ ፡ ነው ። መሬታቸ ውም ፡ በሀብት ፡ በፍሬያማነት ፡ ስመ ፡ ጥር ፡ ነበር ። እርስ ፡ በርሳቸው ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እየተባበሩ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ እየተለያዩ ፡ ለየብቻ ፡ እስከ ፡ ጦርነት ፡ የሚደርሱ ፡ ነገሥታት ፡ ነበሩዋቸው ። የነገሥታቱም ፡ ስም ፡ የአብዛኞቹ ፡

በታችኛው ፡ የግብጽ ፡ (ሜምፌስ) ጣዖት ፡ በጥታህ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ግሪክኛ ፡ በሄ ሊዎስ ፡ (ፀሐይ) ፡ ተሰይሞ ፡ ይገኛል ። የነዚህ ፡ የማክሮባውያን ፡ (መርቄ) ፡ መንግ ሥት ፡ ከግብጽ ፡ ከግሪክ ፡ መንግሥታት ፡ ታሪክቸው ፡ ከታሪክቸው ፡ የነገሥታቱም ዘር ፡ ከነገሥታቱ ፡ ዘር ፡ ጋር ፡ በብዙ ፡ ተደባልቆ ፡ ይገኛል ።

ሰፔኛ ፤ ማቱት ፡ (ማዲት) ፡ በተከዜና ፡ በቀይ ፡ ባሕር ፡ መኸከል ፡ የሚኖሩ ።

ሰፔኛ ፤ ሚጋባር ፡ (ከባዶች) ፡ ወይም ፡ ኒቃኖሪያ ፡ (ድል ፡ አድራጊዎች ፡) የሚባሉ ዛሬ ፡ የባሪያ ፡ ዘር ፡ የሚባሉት ፡ ናቸው ። መልካቸውም ፡ ጥቁር ፡ ቁመታ ቸው ፡ ረጃጅም ፡ ኃይለኞች ፡ የጦር ፡ መሣሪያቸው ፡ አንካሴ ፡ ጦርና ፡ የቆዳ ጋሻ ፡ ነበር ፡ በነሱ ፡ ዘንድ ፡ ሴት ፡ ትልቅ ፡ ክብር ፡ አላት ፤ ሴትን ፡ የመታ ፡ እንደትልቅ ፡ ወንጀለኛ ፡ ይቆጠራል ። አሮጊት ፡ ሴት ፡ የተገኘበት ፡ ጉባዔና ፡ ሽንጎ ሁሉ ፡ የተከበረ ፡ ነው ። በወንድ ፡ ላይ ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ የጭካኔ ፡ ሥራ ፡ ይሠራል ፤ ለምሳሌ ፡ ወገቡ ፡ ጐባጣ ፡ እግሩ አንከሳ ፡ ወይም ፡ የማይድን ፡ በሽታ ፡ ያለው ፡ የተገኘ ፡ (ወይም ፡ የተወለደ ፡) እንደሆነ ፡ ገድለው ፡ ይጥሉታል ። ይኸውም ፡ በነሱ ውስጥ ፡ ያለው ፡ የሁሉም ፡ ሰው ፡ ቁመናው ፡ ያማረ ፡ ሕይወቱ ፡ ጤናማ ፡ የሆነ ብቻ ፡ እንዲገኝ ፡ ነው ። እንደዚህ ፡ ያለው ልማድ ፡ በግሪክ ፡ አገር ፡ በስፓርትና ፡ በኤስ ኪሞ ፤ በአውስትራሊያ ፡ ይገኛል ።

እንደ ፡ ፷ኛው ፡ ቅጥር ፡ ነገዶች ፡ በጣም ፡ አርጅተው ፡ አልሞትም ፡ ያሉትን ፡ አሮጊትና ፡ሽማግሌዎች ፡እበሬ ፡ከርማ ፡ጭራ ፡ ላይ ፡አስረው ፡ እያስገሥቱ ፡ ይገድሏቸዋል። ይኸንን ፡ እምቢ ፡ ያለ ፡ በግድ ታንቆ ፡ ይገደላል ። ሰው ፡ ሲሞት ፡ ጭኑን ፡ ከአንገቱ ጋር ፡ አስረው ፡ እጉብታ ሥፍራ ፡ ላይ ፡ ወስደው ፡ ያስቀምጡና ፡ ጨርሰ ፡ እስኪ ሸፈን ፡ ድረስ ፡ ድንጋይ ፡ ይቆልሉበታል ። በተቆለለው ፡ ድንጋይ ፡ ጫፍ ፡ የጥየል ቀንድ ፡ ይሰኩበታል ።

ሰፔኛ ፤ ሞልዝያ ፡ በዋሻ ፡ የሚኖሩ ፡ ክፍሎች ።

ሰፔኛ ፤ ሞኖፖድ ፡ አንድ ፡ እግር ፤ ሞኖክል ፡ አንድ ፡ ክንድ ፤ ሞኖሴል ፡ አንድ ጭን ፡ ብቻ ፡ ያላቸው ፡ እባብ ፡ የሚበሉ ፡ (አንድ ፡ ክንድ ፡ አንድ ፡ ጭን አንድ ፡ እግር ፡ ብቻ ፡ ነበራቸው ፡ ሲል ፡ የተረት ፡ አነጋገር ፡ ይመስላል ።)

ሰፔኛ ፤ ሞስኮፋጅ ፡ የበሬ ፡ ሥጋ ፡ የሚመገቡ ፡ በሱአኪንና ፡ በአቦክ ፡ መኸ ከል ፡ የሚኖሩ ።

ሰፔኛ ፤ ሚአሴፋል ፡ (ቀንድ ፡ አውጭ ፡ የሚመስሉ ፡ ወይም ፡ የሚገቡ ።)

ሰፔኛ ፤ ኖብያ ፡ ኑብያ ፡ ኖባት ፡ በዛሬው ፡ ጎርዶፋን ፡ የሚገኙ ፡ ከፒግሜይ ፡ (አጫጭር ፡ ሰዎች ፡) ዘር ፡ የወረዱ ፡ ውሽን ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ እንስሳ ፡ የሚያከብሩ ።

ሰኛ ፤ አኖሴፋል ፡ (ከፊታቸው ፡ የአህያ ፡ ጭንቅላት ፡ የሚመስሉ ፡) በኢትዮጵያ ፡ ደቡብ ፡ በኩል ፡ የሚኖሩ ፡ አህያን ፡ ለመዝመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ለጭነት ፡ ለክርቻ ፡ ያሠለ ጠኑ ፡ በአገራቸው ፡ ብርጉድና ፡ ዕጣን ፡ የሚገኝ ፡ በጐናቸው ፡ እንደሚገኙት ፡

ፒግሚ ፡ በበሬና ፡ በዝሆን ፡ ተቀምጠው ፡ የሚሄዱ ። በመኻከላቸው ፡ ሰውን ፡ የሚ በላ ፡ (ጭራቅ ፡) ይገኛል ። ወንጀለኛ ፡ ሲሞት ፡ እንደቅጣት ፡ እንደወርደት ፡ እን ዲቆጠር ፡ በመሬት ፡ ውስጥ ፡ ይቀብሩታል ። የቀረውን ፡ ደህናውን ፡ ሰው ፡ ግን ፡ በእሳት ፡ ያቃጥሉታል ። ምግባቸው ፡ እንቁራሪት ፡ (ባትራክፋሺ) ፡ ስጋቸው ፡ ሴሌኒት ፡ ሉኔሪያን ፡ ይባላል ።

ሟዥኛ ፡ ፋሊሺ ፡ የዛሬው ፡ ፈላሾች ።

ሟዥኛ ፡ ፒግሚ ፡ ቁመታቸው ፡ አንድ ፡ ክንድ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ቅልጥም ፡ ወይም ፡ ሦስት ፡ መዳፍ ፡ የሚሆን ፡ መልክቸው ፡ ጥቁሮች ፡ ጠማሞች ፡ ራቁታቸውን ፡ የሚ ሄዱ ፡ በዝሆንና ፡ በበሬ ፡ ተቀምጠው ፡ የሚጓዙ ፡ በዝሆን ፡ የሚያርሱ ፡ በአትባራ ወንዝና ፡ በጋላባት ፡ ተራራ ፡ መካከል ፡ የሚኖሩ ፡ ናቸው ። ቁጥራቸው ፡ አምስት መቶ ፡ ሺህ ፡ ይደርሳል ። ዛሬ ፡ በአፍሪካ ፡ መካከል ፡ በኮንጎ ፡ ወንዝና ፡ በማዳስካር ይገኛሉ ፡ (በሽማን ፡) አቦሽማኒ ? የሚባሉትም ፡ ቀጥራቸው ፡ ወደነዚሁ ፡ ነው ።

ሟቮኛ ፡ ራብሲ ፡ ከመርዌ ፡ ከደቡብ ፡ በኩል ፡ የሚኖሩ ።

ሟዥኛ ፡ ሪዘፋሺ ፡ ሥራ ፡ ሥር ፡ የሚበሉ ፡ በአትባራ ፡ ወንዝ ፡ በረሀ ፡ የሚ ኖሩ ፡ የበረሀ ፡ ዝንብ ፡ እየነደፈ ፡ በሚያስቸግራቸው ፡ ጊዜያት ፡ ወደ ፡ ረግረግ ፡ ቦታ ሄደው ፡ ተደብቀው ፡ የሚኖሩ ።

ሟዥኛ ፡ ሣምብር ፡ የጋማና ፡ የቀንድ ፡ ከብታቸውን ፡ የቤት ፡ እንስሳቸውን ፡ ሁሉ ፡ ጆሮ ፡ እየቆረጡ ፡ በማሰደግ ፡ ስመ ጥሮች ፡ ናቸው ።

ሟዥኛ ፡ ሳክሲማን ፡ (የዛሬው ፡ ሳሳናብ ፡ ናቸው ።)

የቀሩት ፡ ደግሞ ፡ጸሐፊዎች ፡የአገር ፡ካርታ ፡እየጨመሩ ፡የአገር ፡ ልማድ ፡ እየጠቀሱ ፡ የሚጽፉ ፡ እንደ ፡ ስትራቦን ፡ ያሉት ፡ ሞልተዋል ። የነሱም ፡ ጽሑፍ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም እንደአልነው ፡ የኢትዮጵያን ፡ የጥንት ፡ ታሪክ ፡ ከሥሩ ፡ እንጽፋለን ፡ ብለው ፡ የተ ነሡት ፡ ሁሉ ፡ጀምስ ፡ ብሩስ ፡ ዋሊስ ፡ ባጅ ፡ ጃን ፡ ሞሪዮ ፡ ዣን ፡ ባቲስት ፡ ኩልቦ ፡ ከኒቲ ፡ ሮሲኒ ፡ ..... እየጠቀሱ ፡ ጽፈውት ፡ ይገኛል ።

እነዚህ ፡የጥንት ፡ጸሐፊዎች ፡በዚህ ፡ዓይነት ፡በዘመኑ ፡ቋንቋቸው ፡ በግሪክኛ ፡ ጽፈው ፡በን ገድ ፡ በልማድ ፡በታትነው ፡የሚያሰዩንን ፡ ሕዝብ ፡ በኛ ፡ወገን ፡ያለው ፡ጽሑፍ ፡የነገደ ፡ ክም ፡ ወገኖች ፡ በሆኑ ፡ ነገሥታት ፡ እየተመሩ ፡በደንብ ፡የሚተዳደሩ ፡መሆናቸውን ፡ ከሚያሰየን ጋር ፡ አሳቡ ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ ይጣላል ። ባለፈው ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ እንደአየነው ያገራችን ፡ ጽሑፍ ፡ (ያለቃ ፡ ታዬም ፡ የብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኅሩይም) ፡ ለነገሥታቱ ፡ ስም ፡እየጠቀሰ ፡ የግዛቱን ፡ዘመን ፡እየወሰነ ፡አከታትሎ ፡ ሲያመጣው ፡ የቀረው ፡ ሰፊው ፡ አገር ፡ እንኳን ፡ በይሆን ፡ ሰሜናዊው ፡ኢትዮጵያ ፡በንድ ፡ ክማዊ ፡በሆነ ፡ንጉሥ ፡ የሚተ ዳደር ፡ አስመስሎታል ። የነዚህ ፡ የግሪክቹና ፡ የሮማው ያኖቹ ፡ የታሪክ ፡ ምንጭ ፡ ለየብቻው ፡ በየጐሰው ፡ መልኩን ፡ ልማዱን ፡ ዕምነቱን ፡ ምግቡን ፡ ልብሱን ፡ እየ ለያየ ፡ ለየብቻው ፡ የሚኖር ፡ አስመስሎታል ፡ እንጂ ፡ ሁሉንም ፡ በንድ ፡ ንጉሥ ፡

በንድ ፡ ሥልጣኔና ፡ ልማድ ፡ ጠቅልሎ ፡ አያሳይም ። ናዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሕዝብ ፡ ምንም እንኳን ፡ ኃይለኛ ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ ፡ መጠቅለሉ ፡ በይቀር ፡ በጠፋ ፡ ጊዜ ፡ ተበታትኖ ፡ ለየብቻው ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ በራሱ ፡ ቀንደኛ ፡ በላበት ፡ ብቻ ፡ መተዳደርን ፡ መውደዱ ፡ አይቀርምና ፡ የግሪክቹን ፡ ጸሐፊዎች ፡ ሀሳብ ፡ ሠሙሉ ፡ መቀበልም ፡ ቅር ፡ ቢያሰኝ ፡ በሙሉ ፡ መተውም ፡ አይቻልም ። ነገር ፡ ግን ፡ ጠንዚዛ ፡ አሞራ ፡ ጉማሬ ፡ ..... ፡ የሚመሳሰሉ ፡ ወይም ፡ እየተመገቡ ፡ የሚኖሩ ፡ በለአንድ ፡ ጭን ፡ አንድ ፡ ክንድ ፡ ብለው ፡ ለጸፉት ፡ ከሰውነት ፡ አርዓያና ፡ አምሳል ፡ የራቁ ፡ ስለሚያስመስሉት ፡ አጻጻፋቸው ፡ ተረትና ፡ ቀልድ ፡ የተደበለቀበት ፡ ይመስላል ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ እነዚህ ፡ ሕዝቦች ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ኑሮአቸው ፡ ኃይለኛ ፡ ሲገኝ ፡ እየተሰበሰቡ ፡ ሲጠፉ ፡ በገሳቸው ፡ እንደ ፡ አለቃ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ንጉሥ ፡ እየአበጁ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ እየተዋጉ ፡ እየታረቁ ፡ በዙረት ፡ ሥፍራ ፡ ለሥፍራ ፡ እየተለዋወጡ ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። ከነዚህ ፡ ውስጥ ፡ የግብፅ ፡ የፒራሚድና ፤ የሐውልት ፡ ሥራ አስመርረዋቸው ፡ ከሸማምንት ፡ አምልጠው ፡ በአዳሊስ ፡ የተቀመጡት ፡ የቀሩት ፡ ደግሞ ፡ ከብቢሎንና ፡ ከአሶር ፡ ሥልጣኔን ፡ ይዘው ፡ በያቡብ ፡ ዓረብ ፡ ቆይተው ፡ ከዚያ ፡ በኋለኛው ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተሸግረው ፡ የተቀመጡት ፡ በሥልጣኔ ፡ ከሌሎች ፡ ነገዶች ፡ በመሻላቸው ፡ እንደ ፡ ቅጥር ፡ ያለ ፡ ከተማ ፡ እየከተሙ ፡ ሬደል ፡ አበጅተው ፡ ቋንቋቸውን ፡ ለይተው ፡ የሚኖሩ ፡ እንደ ፡ ሳባውያን ፡ እንደ ፡ ሀበሳን ፡ ያሉት ፡ አሉባቸው ። ሌላውንም ፡ ነገድ ፡ ለመግዛት ፡ የበላይነት ፡ ያሳዩ ፡ እነዚሁ ፡ ሰያሆኑ ፡ አይቀሩም ። ነገር ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ሬት ፡ ተጽፎ ፡ እንደምናገኘው ፡ በኮሰይ ፡ ከአትበራ ፡ ወዲያ ፡ ያሉት ፡ የኑብያ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ከሺህ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ወዲህ ፡ በግብያች ፡ ተገዝተው ፡ ኢትዮጵያውያንም ፡ በ፫፻ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ መልሰው ፡ ግብያችን ፡ የገዙበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ። ነገር ፡ ግን ፡ እነዚህ ፡ ግብፅን ፡ መልሰው ፡ የገዙት ፡ የኑብያ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ እንጂ ፡ ሳባውያንና ፡ ሀበሳን ፡ አይደሉም ። ሳባውያንና ፡ ሀበሳን ፡ ከየመን ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሰሜን ፡ የገቡበት ፡ ጊዜ ፡ የዛሬ ፡ ሊቃውንትና ፡ መርማሪዎች ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ቢበዛ ፡ ፰፻ ፡ ዓመት ፡ ግድም ፡ ላይ ፡ አድርገውታል ። ከዚያ ፡ በፊት ፡ ሥልጣኔና ፡ ሬደል ፡ የሌላቸው ፡ ሳባውያን ፡ ገብተው ፡ እንደሆነ ፡ አይታወቅም ።

እስከ ፡ ዚህ ፡ ጊዜ ፡ እስከ ፡ ሺህ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ግን ፡ የኑብያ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከግብፅ ፡ ጋር ፡ ንግዳቸውን ፡ በሰላም ፡ ይቀጥሉ ፡ ነበር ፡ የንግዱም ፡ ዓይነት ፡ ሬጣን ፡ ከርቤ ፡ ሩርጉድ ፡ የዝሆን ፡ ጥርስና ፤ የአውራሪስ ፡ ቀንድ ፡ ፤ የአውሬ ፡ ቆዳ ፡ ለቤተ ፡ መቅደስና ፡ ለቤተ ፡ መንግሥት ፡ የሚያገለግል ፡ እንጨትና ፡ ባርያ ፡ ሌላም ፡ ይሸን ፡ የመሰሰለ ፡ ነው ።

በ፲፯፻፱ዓ.ም–፲፰፻፭ዓ.ም ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ የአምስተኛው ፡ ዲናስቲ ፡ የግብፅ ፡ ንጉሥ ፡ ነፈርቃል ፡ በነገሠ ፡ በአራተኛው ፡ ዓመት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ (ከኩሽ አገር) ፡ ውስጥ ፡ ድንክየዎች ፡ የኔን ፡ ቤተ ፡ መንግሥትና ፡ የሐጸርን ፡ (ሐትሐር ፡ ሔት ፡ ጣያት) ፡

ቤተ ፡ መቅደስ ፡ በጭፋሮ ፡ በዘፈን ፡ ደስ ፡ እንዲያሰኙ ፡ ይዘህልን ፡ ና ፡ ብሎ ፡ ሐረሐዋይ ፡ ለሚባለው ፡ ሹም ፡ ደብዳቤ ፡ ጽፎለት ፡ ይገኛል ። በደብዳቤውም ፡ ላይ፡ እነዚህን ፡ ድንክዬዎች ፡ ከአገራቸው ፡ ይዘህ ፡ ስትመጣ ፡ በመንገድ ፡ እንዳይጠፉ፡ በመርከብ ፡ አድርገህ ፡ በጉዞም ፡ ጊዜ ፡ ባሕር ፡ እንዳይገቡ ፡ ሴሊት ፡ አሥር ፡ አሥር ፡ ጊዜ ፡ እየተነሣህ ፡ እየፈተሽህ ፡ በጥንቃቄ ፡ ይዘህ ፡ አምጣልኝ ። ለኔ ፡ ከዕንቁም ፡ ከወርቅም ፡ ይበልጥ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝኝ ፡ እነዚህን ፡ ድንክዬዎችን ማግኘት ፡ ነው ። ይሽንን ፡ ስታደርግ ፡ ለልጅ ፡ ልጅህ ፡ የሚተላለፈው ፡ የምሰጥህ ሽልማት ፡ ትልቅ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ ጨምሮ ፡ ገልጸለታል ።

እንግዲህ ፡ እነዚህ ፡ ሁለት ፡ የግብፅና ፡ የኑብያ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የጥንት ፡ መን ግሥቶች ፡ ለየብቻ ፡ ንግድና ፡ ሥልጣኔ ፡ እየተለዋወጡ ፡ ሲኖሩ ፡ የአምልኮአቸ ውም ፡ ዓይነት ፡ ፀሐይዋን ፡ ወርካውን ፡ ተራራውን ፡ ወንዙን ፡ (ዓባይን) ፡ አሞራን ፡ በማምለክ ፡ ይመሰሰላል ። ለነዚህም ፡ የሚያቀርቡት ፡ የእንስሳና ፡ የአዝርእት ፡ መሥ ዋዕት ፡ ይቀራረባል ። ነገሥታቶቻቸውንም ፡ እንደ ፡ አምላክ ፡ እያዩ ፡ በማክበር ፡ ይገናኛሉ ። በተረፈ ፡ ከቤት ፡ መሣሪያ ፡ ውስጥ ፡ ቢላዋው ፡ ምጣዱ ፡ ደማው ፡ ማረ ሻው ፡ የጦር ፡ መሣሪያው ፡ እንካሴው ፡ ጦሩ ፡ ሾተሉ ፡ ይመሰሰላል ።

እነዚህ ፡ ሁለቱ ፡ የግብፅና ፡ የኑብያ ፡ አገሮች ፡ እስከ ፡ እዚህ ፡ እስከ ፡ ሺህ ፡ ስድ ስት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ድረስ ፡ በጉርብትና ፡ በሰላም ፡ ሲኖሩ ፡ ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ የውጭ ፡ ወረራ ፡ እንደአጠቃቸው ፡ እነሆ ፡ እንመለከታለን ።

በፂሺፏ ፡ በፅሺፏያ ፡ መካከል ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ስሙን ፡ ያነሣነው ፡ ራማ ፡ (የማጋዳና ፡ የአዮዲያ ፡ ግሐራጆ) ፡ የሚባለው ፡ የሕንድ ፡ ንጉሥ ፡ ሕንድን ፡ ሰይላ ንን ፡ ዓረብን ፡ ፋርስን ፡ ከለዳውያንን ፡ አሸንፎ ፡ ግብፅን ፡ ወረረ ። የግብፅ ፡ ንጉሥ ፡ ሲዋጋ ፡ ሞተ ። ተክታዮቹም ፡ መዋጋት ፡ የማይጠቅም ፡ መሆኑን ፡ ሲረ ዱት ፡ ገበሩ ። እንደዚሁም ፡ ይሽው ፡ የሕንድ ፡ ንጉሥ ፡ ራማ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንዳልነው ፡ ከነገደ ፡ ካም ፡ ውስጥ ፡ ጲአሪ ፡ ኣንደኛ ፡ በነገሠበት ፡ ዘመን ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መጥቶ ፡ ጲአሪን ፡ ወግቶ ፡ መንግሥቱን ፡ ያዘበት ። በኋላ ፡ ነገደ ፡ ዮቅ ጣን ፡ አክናሁስ ፡ ሰባ ፡ ሁለተኛን ፡ መሪ ፡ አድርገው ፡ የራማን ፡ ንጉሥ ፡ ተዋግ ተው ፡ ገደሉት ፡ ሲል ፡ ባንዳንድ ፡ የውጭ ፡ አገርም ፡ በአገራችንም ፡ ታሪክ ፡ ነገሥት ፡ ተጽፎ ፡ ይገኛል።ነገር ግን በዚህ ፡ ዘመን ፡ ራማ ፡ የሚባል ፡ የሕንድ ፡ ንጉሥ የግብፅን ፡ ንጉሥ ፡ ገድሎ ፡ አገሩን ፡ ገዛ ፡ የሚል ፡ በግብፆች ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ አይገኝም። ከፂሺ ፡ እስከ ፡ ፅሺፏያፒፓ ፡ ድረስ ፡ በፅፂኛው ፡ ሥርወ መንግሥት ፡ ተመሥ ርተው ፡ ግብፅን ፡ ያስተዳድሩ ፡ የነበሩት ፡ የቱብ ፡ ዘር ፡ የሆኑት ፡ ነገሥታት ፡ እሜኔም ሐት ፡ ፅኛ ፡ ሳኑስትሪ ፡ ፅኛ ፡ (ሴሶስትሪስ) ፡ አሜኔምሐት ፡ ፂኛውና ፡ ፫ኛው ፡ ሳኑ

ስትሪ ፡ ይኖው ፡ በሚገዙበት ፡ በሁለት ፡ ሺና ፡ በሺኀያ፻ ፡ ዓመት ፡ መከከል ፡ ራማ ፡ የሚባል ፡ የሕንድ ፡ ንጉሥ ፡ ገዛቸው ፡ የሚል ፡ የለም ። ከ፩ሺኀያ፻ ፡ እስከ ፡ ፩ሺ ፭ያ፻ ፡ በለው ፡ የመቶ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ፡ ከዚህ፡ ቀደም፡ የጠቀስናቸው ፡ የሂክሶስ፡ ዘሮች፡ ወደሬት ፡ እንደምናገኘው ፡ ግብፅን ፡ ገዝተዋል ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ከነርሱ ፡ ውስጥ ፡ ራማ ፡ የሚሉ ፡ የሕንድ ፡ ንጉሥ ፡ የለም ።

በንድ ፡ ወገን ፡ ደግሞ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ አንዳንድ ፡ ጸሐፊ ፡ ራማን ፡ ተዋግተው ፡ የገደሉ፡ ሒክሶስ ፡ የሚባሉ፡ ከምሥራቅ ፡ የመጡ ፡ ኃይለኛ ፡ ሕዝቦች ፡ የነበሩ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የነበሩ ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ወይም ፡ የነገደ ሳባ ፡ ዘሮች ፡ አይደሉም ፡ የሚሉ ፡ አሉና ፡ ስለራማ ፡ ወደፊት ፡ እስኪጣራ ፡ ድረስ ፡ እንዳለ ፡ እንተወው ።

ግማሾቹም ፡ ሒክሶስ ፡ የተባሉት ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ አይደሉም ፡ የሚሉ ፡ ግማሾቹም ፡ ሒክሶስ ፡ የተባሉት ፡ እነዚያው ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ናቸው ፡ የሚሉ ፡ አሉ ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ስማቸው ፡ ሒክሶስ ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ እየተባለ ፡ ቢለያይም ፡ ሁለቱም፡ የመጡበት ፡ ሥፍራ ፡ ያው ፡ ምሥራቅ፡ ዘራቸውም፡ ሁለቱም ፡ ሴማዊ ፡ ስለሆነ ፡ ነገሩ ፡ ተያይዘ ፡ ይገኛል። ምናልባት፡ ነገደ ፡ ዮቅጣንም ፡ ሒክሶስም ፡ የዘራቸው ፡ ግንድ ፡ ያው፡ ዮቅጣን ፡ ሆኖ ፡ ሒክሶስ ፡ በላይ ፡ በሰሜን ፡ በሶርያ ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ግብፅ ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ የምንላቸው ፡ በታችኛው ፡ ዓረብ ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ገብተው ፡ ይሆናል ።

እነዚሁም ፡ ሒክሶስ ፡ የሚባሉት፡ ዘሮች፡ መቶ፡ ዓመት፡ ግብፅን ፡ ገዝተው፡ ሲወጡ ፡ ነገደ፡ ዮቅጣን፡ ግን፡በኢትዮጵያ፡ ተመሥርተው ፡ መቅረታቸውን ፡ እንጂ ፡ ተመልሰው ፡ ወጡ ፡ የሚል ፡ ታሪክ ፡ የለምና ፡ ሁለቱ ፡ የተለያዩ ፡ የነገድ ፡ ቅርንጫፎች ፡ መሆናቸውን ፡ ይኸም ፡ የሚያስረዳ ፡ ይመስላል ። ነገር ግን ፡ ዘሩ ፡ አንድ ፡ ሆኖ ፡ ቅርንጫፉ ፡ ለየብቻ ፡ የሆነ ፡ ሁለት ፡ ነገድ ፡ ለየብቻ ፡ በሁለት ፡ አገር ፡ ገብቶ ፡ በግዛት ፡ ከኖረ ፡ በኋላ ፡ እንደኛው ፡ ተሸንፎ ፡ መውጣት ፡ እንደኛው ፡ ተመሥርቶ፡ መቅረት ፡ የተለመደ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ከምሥራቅና ፡ ይልቁንም ፡ ከወደ ፡ አሶር ፡ መጥተው ፡ ግብፅን ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ የገዙት ፡ ሒክሶስ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በግብፅ ፡ ሕዝብ፡ ላይ ፡ የጭቆና ፡ ሥራ ፡ ስለአሳዩ ፡ ሕዝቡና ፡ ሹማምንቱ ፡ ጠልተዋቸው ፡ የሚያስወጡበትን ፡ ጊዜና ፡ መንገድ ፡ ይፈልጉ ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ገሸዎቹ ፡ ሒክሶስ ፡ አብዛኛው፡ መቀመጫቸው፡ በሰሜናዊ፡ ግብፅ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ የደቡብን፡ ሕዝብ፡ ክፍል ፡ በደንብ ፡ ለመቆጣጠር ፡ አልቻሉም ፡ ነበርና ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ያሉት ፡ የግብፅ ፡ መሳፍንትና ፡ ሕዝብ ፡ በሰሜን ፡ ያሉትንም ፡ ወገኖቻቸውን ፡ እየቀሰቀሱ ፡ አንድነት፡ ተዘጋጅተው ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ተገዘው ፡ ሒክሶስን ፡ ተዋግተው ፡ ከአስወጡ ፡ በኋላ፡ የራሳቸውን ፡ መንግሥት ፡ መልሰው ፡ አቆሙ ።

የነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ግን ፡ ሁኔታው ፡ እንደታሪኩ ፡ ከሒክሶስ ፡ የተለያየ ፡ ነው ። ነገደ፡ ዮቅጣን ፡ መገሥሪያ ፡ በምሥራቅ ፡ ምናልባት ፡ በባቢሎን ፡ ሲኖሩ ፡ የባቢሎንን ፡ ሥልጣኔ ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ዓረብ ፡ መጡ ። በደቡብ ፡ ዓረብም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ፡

ከተቀመጡ ፡ በኋላ ፡ ሕንዶች ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ሕዝብ ፡ እየወጉ ፡ ስለአስቸገሩዋቸው ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ በፈቃዳቸው ፡ ለምለም ፡ አገር ፡ ፍለጋ ፡ ይሁን ፡ ከደቡብ ፡ ዓረብ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሰሜን ፡ ተሻግረው ፡ ተቀመጡ ።

ከዚያም ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ግማሾቹ ፡ በትግሬ ፡ ግማሾቹ ፡ በአዳል ፡ ግማሾቹ ፡ በውጋዴን ፡ አገር ፡ ተከፋፍለው ፡ በሰላም ፡ ሲኖሩ ፡ እንደባላገር ፡ ይኸም ፡ ቢቀር ፡ እንደ ፡ መልክም ፡ እንግዳ ፡ ይቆጠሩ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ ሐክሶስ ፡ በግብፆች ፡ እንደተጠሉ ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ የአገር ፡ ተወላጅነት ፡ ባለው ፡ በነገደ ፡ ክም ፡ ዘንድ ፡ የተጠሉ ፡ አይመስልም ። ተግሸ ፡ የባዕድ ፡ ገሸን ፡ መጥላቱ ፡ ገሸም ፡ እየገበረ ፡ በሰላም ፡ የሚቀመጠውን ፡ አለመጥላቱ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። የሩቁን ፡ ዘመን ፡ የሚተርከው ፡ የዘሬው ፡ ታሪክ ፡ ነገሥታችን ፡ የሚለው ፡ አርግጥ ፡ እንደሆነ ፡ የሀገድ ፡ ንጉሥ ፡ ራማ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መጥቶ ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ የነበረውን ፡ ንጉሥ ፡ ኤአሪን ፡ ወግቶ ፡ ኢትዮጵያን ፡ በስገበረ ፡ ጊዜ ፡ እነዚሁ ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ከያለበት ፡ ተሰብስበው ፡ ከመከከላቸው ፡ አክናሁስን ፡ አንግሠው ፤ የሕንዱን ፡ ንጉሥ ፡ ራማን ፡ ተዋግተው ፡ ስለአስወጡ ፡ ነገደ ፡ አጋዓዝያን ፡ (ነፃ ፡ አውጭዎች) ፡ የሚባል ፡ ስም ፡ ተሰጣቸው ።

ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ ነፃ ፡ ባወጡት ፡ አገር ፡ በነገደ ፡ ክም ፡ ነገሥታት ፡ ምትክ ፡ ገብተው ፡ መንግሥታቸውን ፡ መሠረቱና ፡ የነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ሕዝብ ፡ ከነገደ ፡ ክም ፡ ዘር ፡ ጋር ፡ ተደበልቀው ፡ ይኖሩ ፡ ዝመር ፡ ማለት ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ በኢትዮጵያ ፡ የቆየው ፡ የክም ፡ ሕዝብ ፡ ከደቡብ ፡ ዓረብ ፡ የመጣው ፡ የዮቅጣን ፡ ሕዝብ ፡ በልማድ ፤ በወግና ፡ በሥርዓት ፡ በአምልክ ፤ በቋንቋ ፡ መለያየታቸው ፡ የታወቀ ፡ ስለሆነ ፡ ከመርዌ ፡ እስከ ፡ ኤርትራ ፡ ባሕር ፡ ባለው ፡ በሰፈው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ምድር ፡ እየተለያዩም ፤ እየተገናኙም ፡ ኃይለኛ ፡ ሆኖ ፡ ለነገሠው ፡ እየገበሩ ፡ ያም ፡ ሲጠፋ ፡ እየተለያዩ ፡ በየነገዳቸው ፡ እንደልማዳቸው ፡ መኖራቸው ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ከመከከላቸው ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ሥልጡኖችና ፡ ጽሑፍ ፡ ያላቸው ፡ ናቸው ፡ ቢባልም ፡ ይህ ፡ አስካሁን ፡ የተገኘው ፡ ጽሑፍ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንዳልነው ፡ ዘመኑ ፡ በግምት ፡ ከጀሮ ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ነውና ፡ ምና ልባት ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ ፊደል ፡ የሌለውና ፡ ያልሠለጠነ ፡ የሴምና ፡ የዮቅጣን ፡ ዘር ፡ መጥቶ ፡ ከክሙና ፡ ከኩሽ ፡ ጋር ፡ ተደበልቆ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንደተባለው ፡ በዘሬይቱ ፡ ኢትዮጵያና ፤ በጥንታዊቲቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በኑብያ ፡ (ሱዳን) ፡ ጭምር ፡ ሲኖሩ ፡ የነገዳቸውን ፡ ዝርዝር ፡ ስም ፤ የሚቀመጡበትን ፡ ሥፍራ ፡ የሚመገቡትን ፡ እንሰሳ ፤ ይነስ ፡ ይብዛ ፡ እንደ ፡ አጋርታሺድ ፡ እውነትም ፡ ስሕተትም ፡ የተደበለቀ ፡ ቢይጠፋበት ፡ እነሆ ፡ ባለፈው ፡ ተመልክተናል ። ከዚህ ፡ በተረፈ ፡ ደግሞ ፡ እነዲዮዶር ፡ ከጻፋት ፡ ከጥንታውያኑ ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ ልማድ ፡ የለቀምን ፡ እንደሆነ ፡ ከዚህ ፡ የሚከተለው ፡ ምዕራፍ ፡ የሚያስረዳንን ፡ እናገኛለን ።

ምዕራፍ ፡ ፬ ።

በሰላም ፡ ጊዜ ፡ ንግድ–በወርነት ፡ ጊዜ ፡ ሲዋጉ–ንጉሥና ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ያገር ፡ ልማድ–ሃይማኖት ፡ –ጋብቻ ።

ይኸው ፡ የክምና ፡ የሴም ፡ ዘር ፡ የሠለጠነው ፡ የሳባና ፡ የሀብሳን ፡ ዘር ፡ ከደቡብ ፡ ዓረብ ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ በጀሮ ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ግድም ፡ መጥቶ

ደምበኛ ፡ ሥልጣኔውን ፡ እስኪተክል ፡ ድረስ ፡ ከተከለም ፡ በኋላ ፡ ከኩብያ ፡ ወዲያህ ፡ ዝምሮ ፡ እስከ ፡ ኤርትራ ፡ ያሉት ፡ ሕዝቦች ፡ ያላቸውን ፡ የንግድ ፡ የልማድ ፡ የሃይማኖትና ፡ የጦርነት ፡ ሁኔታ ፡ ከዚህ ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

ንግድና ሸቀጥ ።

የሸቀጡ ፡ ዓይነት ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንደጻፍነው ፡ ዕጣን ፡ ከርቤ ፡ እንጨት ፡ የአውሬ ፡ ጥርስና ፡ ቀንድ ፡ በርያ ፡ ደግሞ ፡ ከምሥራቅ ፡ የመጡት ፡ ሥልጡኖቹ ፡ ልብስ ፡ ሽቱ ፡ እንደ ፡ አንበር ፡ እንደ ፡ ዶቃ ፡ ያለ ፡ ጌጣጌጥ ፡ አያጡም ። ሸቀጥ ፡ ለሸቀጥ ፡ ሲገበያዩ ፡ መለኪያቸው ፡ ዛሬም ፡ በባላገር ፡ ሲደረግ ፡ እንደምናየው ፡ ክንድ ፡ መዳፍ ፡ ጣት ፡ ነው ። በተረፈ ፡ እንደ ፡ መቃ ፡ እንደ ፡ ዘንግ ፡ ያለ ፡ መለኪያ ፡ አላቸው ። እንደ ፡ እህል ፡ የመሰለውንም ፡ የሚሉኩበት ፡ የሸክላ ፡ ማሰሮና ፡ አንዳንዱቹም ፡ የነሐስ ፡ ማሰሮ ፡ የመሰለ ፡ ነበራቸው ። ይኸም ፡ ሁኔታ ፡ እነሆ ፡ መሻሻል ፡ በላገኙ ፡ ባላገሮቻችን ፡ ዘንድ ፡ ዛሬም ፡ ሲሠራበት ፡ ስለምናይ ፡ እንደ ፡ ዘመኑ ፡ ርቀት ፡ የመጣሪያውና ፡ የሸቀጡ ፡ ዓይነት ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ ሊያስደንቀን ፡ አይችልም ።

በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ሲዋጉ ።

ሁለት ፡ ነገድ ፡ ሲጣላ ፡ ሁለቱም ፡ የጠላት ፡ ወገኖች ፡ ወደ ፡ ጦርነቱ ፡ ሥፍራ ፡ ጉዞ ፡ ያደርጋሉ ። በጉዞ ፡ ንጉሣቸው ፡ የሚማሸቹ ፡ በሠረገላው ፡ ላይ ፡ ተቀምጠ ፡ (ጋሪውን) ፡ ከፊት ፡ እንስሳ ፡ ወይም ፡ ሰው ፡ እየጐተተው ፡ የሚማሸ ፡ ንጉሥ ፡ በመሐል ፡ በእግሩ ፡ ወይም ፡ በክብት ፡ እየተጓዘ ፡ በዘፈን ፡ በጭፋሮ ፡ ወደ ፡ ጦርነቱ ፡ ቦታ ፡ ይኼዳል ። ጦርነቱም ፡ ሊጀመር ፡ አቅራቢያ የሰውን ፡ ልብ ፡ ለመቀስቀስ ፡ ጭፋሮው ከፊተኛው ፡ ይደምቃል ። በሁለቱም ፡ እጅ ፡ ያለው ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ በትንሹ ፡ ይለያያል ፡ እንጂ ፡ አብዛኛ ፡ ጊዜ ፡ ያው ፡ የታወቀው ፡ ደንጊያ ፡ (የሾለ ፡ ወይም ፡ ስለት ያለው ፡) ቀንድ ፡ ወንጭፍ ፡ አንካሴ ፡ ጦር ፡ ቢላዎ ፡ መጥረቢያ ፡ ቀስት ፡ ፍላጻ ፡ መመከቻው ፡ የቆዳ ፡ ጋሻ ፡ ከጋሻም ፡ በተለይ ፡ ዓይነት ፡ የተሠራ ፡ ነው ። ሙጊ ያው ፡ የሚዝመረው ፡ ከሁሉ ፡ መሣሪያ ፡ በሚረክሰው ፡ በደንጊያ ፡ ነው ። ክሩቅ ፡ ዝምረው ፡ እየተወራወሩ ፡ በተጠጋጉ ፡ ጊዜ ፡ የቀስቱ ፡ ከዚያም ፡ የአንካሴው ፡ የጦሩ በትር ፡ ይቀጥልና ፡ ሲገናኙና ፡ ሰይበለቁም ፡ የቢላዋና ፡ የጩቤው ፡ ሥራ ፡ በተራው ይደርሳል ። መቼም ፡ ሁለት ፡ ወገኖች ፡ ተዋግተው ፡ አንደኛው ፡ መሸነፉ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ጸሩ ፡ ግን ፡ የተሸነፈውና ፡ የተማረከው ፡ ወገን ፡ ወዮለት ። ከምርኮ ፡ ቀን ፡ ዝምሮ ፡ ማናቸውንም ፡ የእብሪት ፡ ሥራ ፡ አሸናፊዎቹ ፡ በተሸናፊዎቹ ፡ ይፈጽመባቸዋል ። ንጉሥ ፡ የነበረው ፡ የአሸናፊውን ፡ ንጉሥ ፡ ሠረገላ ፡ በእግሩ ፡ እየሄደ ፡ መጐተት ፡ የቀረውም ፡ እንደ ፡ ክብት ፡ ቀንበር ፡ ተሸክሞ ፡ በገመድ ፡ የፈጥኝ ፡ መታሠርና ፡ እንደ ፡ ባሪያ ፡ ተቆጥሮ ፡ መሥራት ፡ መዋረድ ፡ መገጠጥ ፡ አለበት ። በዝግንነት ፡ መዋጋቱንም ፡ አውቀው ፡ አሸናፊዎቹ ፡ በልባቸው ፡ ቢያከብሩትም ፡ ከምርኮ ፡ በኋላ ፡ የውርደት ፡ ሥራ ፡ በራሱም ፡ በሚስቱም ፡ በቤተ ፡ ሰቡም ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ይፈጽሙበታል ። የተሸናፊው ፡ ቆንጆ ፡ ሚስት ፡ ወይም ፡ ልጅ ፡ ወዲያው ፡ ያሸናፊው ፡ ሚስቶች ፡ ይሆናሉ ። የቀሩት ፡ ይኸን ፡ የጋብቻ ፡ ዕድል ፡ ያላገኙት ፡ የባርነት ፡ ሥራ ፡ ይሠራሉ ። ሳይዋጋም ፡ በቶሎ ፡ የገበረና ፡ ያመነም ፡ ሲኖር ፡ ከውር

ደት ፡ አይድንም ። እንደ ፡ እንስሳ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ሴት ፡ እየተቆጠረ ፡ መሰደብንና ፡ መወቀስን ፡ ይጨምራል ።

ንጉሥና ፡ አንዳንድ ፡ ያገር ፡ ልማድ ።

እንደ ፡ ዲዎዶር ፡ አጻጻፍ ፡ ግብያች ፡ ንጉሣቸውን ፡ ፈርያን ፡ እንደሚሉት፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ደግሞ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ 2000-700 ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት፡ ንጉሣቸውን ፡ ሱተን ፡ ይሉት ፡ ነበር ። ሱተን ፡ ማለት ፡ በጥንታዊ ፡ የግብፅ ፡ ቋንቋ ፡ የንጉሥ ፡ ልጅ ፡ ወይም ፡ የንጉሥ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ማለት ፡ ነው ። በተረፈ ፡ የኢት ዮጵያውያኖቹ ፡ እንደ ፡ ግብያቹ ፡ ንጉሥ ፡ ከመንገሡ ፡ በፊት ፡ አንድ ፡ ስም ፡ ከነገሠ ፡ በኋላ ፡ ሌላ ፡ ስም ፡ (ስመ ፡ መንግሥት) ፡ ይሰጠዋል ። የዚህም ፡ ልማድ ፡ እነሆ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ሲቀጥል ፡ እናያለን ። ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ የአምላ ክነት ፡ ደረጃ ፡ ሲሰጠው ፡ ከቀድሞዎቹ ፡ አማልክት ፡ ስም ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ አድ ርገው ፡ ሌላ ፡ አዲስ ፡ ስም ፡ ይጨምሩለታል ። እንደዚህ ፡ የበረከተ ፡ ያንድ ፡ ንጉሥ ፡ ስም ፡ በኋለኛው ፡ ጊዜ ፡ በአጻጻፍ ፡ በታሪክ ፡ ውስጥ ፡ እየአሰሰተ ፡ አስቸግሯል ።

ያመራረጣቸው ፡ ወገን ፡ ያንዱ ፡ ነገድ ፡ ከሌላው ፡ መለያየት ፡ አለበት ። ለም ሳሌ ፡ የናፓታና ፡ የመርዌዎቹ ፡ ወገኖች ፡ ንጉሥ ፡ የሚያነግሡት ፡ ከሕዝቡ-ውስጥ፡ መልኩ ፡ ከአምላክቸው ፡ ከአሞን ፡ (አሜን-አሙን) ፡ ምስል ፡ ጋር ፡ የተመሰሰ ለውን ፡ ነው ፡ መራጮቹ ፡ ካህናቱ ፡ ናቸው ። ከተመረጠም ፡ በኋላ ፡ በክብር ፡ ከአ ምላኩ ፡ ጋር ፡ ባይተካከልም ፡ ወደዚያው ፡ ይጠጋል ። የቀሩት ፡ ደግሞ ፡ ከላይ ፡ ሲያያዝ ፡ በባላባትነት ፡ የወረደውን ፡ ወይም ፡ ቀንደኛ ፡ ሆኖ ፡ የተነሣውን ፡ ወይም ፡ ሽግና ፡ ሆኖ ጠላትን የመለሰውን ፡ አገር ፡ በመውረርና ፡ በጉብዝና ፡ የታወቀ ውን ፡ ያነግሣሉ ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ማንኛውም ፡ አብዛኛው ፡ ንጉሥ ፡ ከነገሠበት ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ ወሰን ፡ የሌለው ፡ ክብርና ፡ ሥልጣን ፡ ነበረው ። በነገሠበት ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ከዛሬ ፡ ዘመን ፡ ዲክታተር ፡ ይበልጥ ፡ የልቡን ፡ ይሠራል ። የሚስቶቹ ፡ ቁጥር ፡ ወሰን ፡ የለውም ። ልቡ ፡ ከፈቀደ ፡ እህቱንም ፡ ልጆቹንም ፡ የልጅ ፡ ልጆቹንም ፡ ማግባት ፡ ይችላል ። እንደርሱ ፡ ከጣዖት ፡ ካህናት ፡ በስተቀር ፡ የቀሩት ፡ ሹማምንቱና ፡ ሕዝቡ ፡ ዘመዶቻቸውን ፡ ያገቡ ፡ ነበር ።

ባንድ ፡ ምክንያት ፡ ወይም ፡ በደጋ ፡ የንጉሡ ፡ እጅ ፡ ወይም ፡ እግር ፡ የተቆረጠ ፡ እንደሆነ ፡ ቤተ ፡ ሰቡ ፡ ሁሉ ፡ ከርሱ ፡ ተለይተው ሙሉ ፡ ሰውነት ፡ ይዘው ፡ ደስታ ፡ እንዳያገኙ ፡ እንደልማድ ፡ ሆኖ ፡ በውደም ፡ ዘግድም ፡ የማቆ ረጡ ፡ ነበሩ ። ሲሞት ፡ አብረው የሚሞቱ ፡ አሉ ። ስለዚህ ፡ የንጉሥ ፡ ሕይ ወትና ፡ አካል ፡ የሁሉም ፡ የሕይወት ፡ መሠረት ፡ ስለሆነ ፡ አክብረው ፡ ተጠ ንቅቀው ፡ ይጠብቁታል ።

ያንደኛው ፡ ነገድ ፡ ንጉሥ ፡ ወይም ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ የሞተ ፡ እንደሆነ፡ በአቧራ ፡ እራሳቸውንና ፡ ፊታቸውን ፡ እየፈተጉ ፡ የሚያለቅሱ ፡ እንጂ ፡ እራሳ

ቸውን ፡ የማይገድሉ ፡ አሉ ። የነገዱ ልማድ ፡ ልዩ ልዩ ፡ ነው ። ከወንድ ፡ ንጉሥ ፡ የሴት ፡ ንግሥት ፡ መርጠው ፡ በሴት ፡ የሚገዙ ፡ አሉ ። እነሱም እንደ ፡ ቤግሜይ፡ እንደ ፡ አስማክ ፡ ያሉት ፡ ናቸው ። በመርዌም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንግሥታት ፡ የሚ ባሉ ፡ በሕንደኬ ፡ ስም ፡ የሚጠሩ ፡ ብዙ ፡ ሴቶች ፡ እንደነበሩ ፡ ከሥፍራው ፡ ስንደርስ ፡ እናገኛለን ።

ባለፈው ፡ በዝርዝሩ ፡ እንደ ፡ ሰማነው ፡ አንዱ ፡ ነገድ ፡ በዝሆን ፡ ሌላው፡ በዓጣ ፡ ሥጋ ፡ ሌላው ፡ በጥራጥሬ ፡ እህል ፡ አንዱ ፡ በፍራፍሬና ፡ በዛፍ ሥር፡ ምግብ ፡ የሚኖሩ ፤ አንዱ ፡ በዛፍ ፡ ላይ ፡ አንዱ ፡ በዋሻ ፡ የሚቀመጥ ፤ አንዳ ንዱ ፡ ነገድ ፡ ሰው ፡ ሲሞትበት ፡ አሥሮ ፡ እዛፍ ፡ ላይ ፡ የሚያንጠለጥል ፤ ሌላው ፡ በመሬት ፡ የሚቀብር ፡ ወይም ፡ እሜዳ ፡ ላይ ፡ ጥሎ ፡ ድንጋይ ፡ የሚቆልል ፡ አንዱ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ የሚጨምር ፡ አለ ። ልብሱም ፡ እንደደረጃቸው ፡ ቅጠል፤ ቆዳ ፤ ኬሻ ፤ ልብስ ፡ የሚለብሱ ፡ አሉ ። የጥንት የክም ፡ ወይም ፡ የኩሽ ፡ ነገድ ፡ በየሥፍራው ፡ የሚኖርበት ፡ ሕይወት ፡ ዛሬም ፡ ቢሆን ፤ በአማራም ፡ በትግሬም ፡ ባላገር ይልቁንም ፡ በደቡብ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በአሩሲ ፡ በባሌና ፡ በሌ ላውም ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ በአፍሪካ ፡ በእስያና ፡ በአውስትራልያ ፡ አህጉር ፡ ከሚኖ ረው ፡ ሕዝብ ፡ ሕይወት ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ ልዩነት ፡ ያለው ፡ አይመስልም ። ነገር ፡ ግን ፡ ሥልጣኔን ፡ ከባቢሎንና ፡ ከምሥራቅ ፡ ይዘው ፡ የመጡት ፡ ወይም፡ ከግብፅ ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ በማድረግ ፡ ሥልጣኔን ፡ የተከፈሉት ፡ ወገኖች ፡ ከሌ ላው ፡ ነገድ ፡ በቤትም ፡ ሥራ ፡ በመሣሪያም ፡ በልብስም ፡ በማናቸውም ፡ የኑሮ፡ ደረጃ ፡ ከፍ ፡ ብለው ፡ ይገኛሉ ። መጻፊያ ፡ ሬደልና ፡ ንግግራቸውን ፡ የሚቀ ርጹበት ፡ የሰዋስው ፡ መንገድ ፡ ሁሉ ፡ ነበራቸው ።

ሃይማኖት ።

የቀድሞ ፡ ኢትዮጵያም የሌላውም ፡ አገር ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ ሃይማኖ ትና ስለጋብቻ ፡ ሕግ ስለአልተሰጠው ፡ ራሱ ፡ በአሰበውና ፡ በፈቀደው ፡ መን ገድ ፡ ይኖር ፡ ነበር ። በሥልጣኔ ፡ ዝቅ ፡ ያለው ፡ በዛፍ ፡ በተራራ ፡ ያመልክል ፤ የሠለጠነው ፡ ወገን ፡ አምላክ ፡ መኖሩን ፡ ያምንና ፤ አምላኩን ፡ በሰው ፡ በፀሐይ፡ በጨረቃ ፡ እየመሰለ ፡ ከዚያም ፡ በበሬም ፡ በበግም ፡ በአሞራም. . ሊያድር ፡ ይችላል ፡ በማለት ፡ በነዚሁ ፡ እንስሶች ፡ ምስሉንና ፡ ሐውልቱን ፡ በድንጋይም ፡ በብረትም ፡ በብርም ፡ በወርቅም ፡ እየሠራ ፡ ለአማልክቱ ፡ ምስል ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ እያነጸ ፡ ለቤተ ፡ መቅደሱና ፡ ለአማልክቱ ፡ በየደረጃው ፡ ከህናትና ፡ ነቢያት ፡ አበልና ፡ ደረጃ ፡ እየተወሰነ ፡ የአምልክ ፡ ሥራቸውን ፡ ያከናውናሉ ።

የጥንት ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ አምልክ ፡ ከዚያውም ፡ ከግብፅ ፡ የሚዋሰኑት ፡ የናፓታና ፡ የመርዌዎቹ ፡ አምልክአቸው ፡ ከግብፅ ፡ ይገናኛል ። ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ በመዠመሪያ ፡ ከምን ፡ የኖህን ፡ ልጅ ፡ እንደአምላክ ፡ ያመልኩት ፡ ነበር ፡ ይባላል። ነገር ፡ ግን ፡ በጣም ፡ የታወቁት ፡ አማልክት ፡ አሞን ፤ አሲሪስ ፤ ኑም ፤ ቶት ፤ አሲስ ፤ ሴት፡

ሰቴ ፤ ሐጸር ፤ (ሐትሐር) ሳራፖስ ፥ ናቸው ። ዓባይም ፥ ራስ ፤ ጸሐይም ፥ ራሷ ፥ አማል
ክት ፥ ናቸው ። የተራቀቁት ፥ ደግሞ ፥ ዓባይና ፤ ፀሐይ ፥ ሁለቱም ፥ የአምላክ ይሽሙም ፥
የአሞን ፥ ስጦታ ፥ ስለሆኑ ፥ ግማሽ ፥ አማልክት ፥ ናቸው ፥ ሲል ፥ ያገኛል ። ከክ
ርስቶስ ፥ ልደት ፥ በፊት ፥ ከ፲፯ኛው ፥ መቶ ፥ ዓመት ፥ ዠምሮ ፥ ክርስትና ፥ እስ
ኪሸረው ፥ ድረስ ፥ አሞን ፥ ሁሉን ፥ ደምስሶ ፥ ፀሐይም ፥ ዋናውም ፥ አምላክ ፥
እሱ ፥ ሆኖ ፥ በታላቅ ፥ ክብርና ፥ ግናናነት ፥ በቴብ ፥ በመርዌ ፥ በናፓታ ፥ ሲመለክ
በት ፥ ሲሰገድለት ፥ ኖርዋል ። የርሱንም ፥ አምላክነት ፥ ከዚህ ፥ ሰፋ ፥ ባለ ፥ አኳኋን ፥
ወደ ፥ ፊት ፥ በናፓታው ፥ በፒያንኪና ፥ በታላቁ ፥ ፈርዖን ፥ በራምሲስ ፥ ዘመን ፥
ላይ ፥ ጽፈንለታል ፥

በተረፈ ፥ የአገር ፥ ሕዝብ ፥ በሙሉ ፥ በሕብረት ፥ የሚያከብረው ፥ አንዱ ፥ አው
ራጃ ፥ ከሌላው ፥ ይበልጥ ፥ ለግሉ ፥ የሚወደውና ፥ የማያከብረው ፥ አንድ ፥ አንድ ፥
አምላክ ፥ አለው ። ከሁሉ ፥ ከፍ ፥ ያለችው ፥ ፀሐይ ፥ ግን ፥ በአሞን ፥ ስም ፥ በመ
ላው ፥ ኢትዮጵያ ፥ (መርዌ) ፥ ተከብራ ፥ ይሰገድላት ፥ ነበር ። ከኢትዮጵያ ፥ ሰሜን ፥
ከግብፅ ፥ ደቡብ ፥ ምሥራቅ ፥ የሚገኙት ፥ የብለሜ ፥ (አገው ፥ ?) ሰዎች ፥ የሰው ፥
ቍርባን ፥ ለፀሐይ ፥ ያቀርቡላት ፥ ነበር ፥ ይባላል ። በዋሽ ፥ ነዋሪ ፥ በበረሀ ፥ ተቀ
ማጭ ፥ የተባሉት ፥ ሁሉ ፥ በልዩ ፥ ልዩ ፥ ዓይነት ፥ ፀሐይን ፥ (አሞንራ ፥) ያመልኩ ፥
ነበር ። የመርዌ ፥ ነገሥታት ፥ እንደቴብ ፥ እንደመምፌስ ፥ የግብፆች ፥ ነገሥታት ፥ የአ
ሞንራ ፥ (የፀሐይ) ፥ ካህናት ፥ ሲሆኑ ፥ ሚስቶቻቸው ፥ ደግሞ ፥ የሙት ፥ (የጨ
ረቃ) ፥ ካህንነት ፥ ነበራቸው ።

ጋብቻ ።

በዚህ ፥ ዘመን ፥ ሕዝቡ ፥ ሁሉ ፥ የያሬትና ፥ የክርስትና ፥ የቡድሀ ፥ ወይም ፥
የእስላም ፥ ሕግ ፥ ስለሌለው ፥ ነገሥታቱም ፥ ሹማምንቱም ፥ ሕዝቡም ፥ ብዙ ፥
ሚስት ፥ ያገባሉ ። ከባዕድ ፥ ወገን ፥ ካገቡ ፥ በኋላ ፥ አባታቸው ፥ የሞተ ፥ እንደ
ሆነ ፥ እናታቸውን ፥ እህታቸውን ፥ ልጃቸውንም ፥ ሊያገቡ ፥ ይችላሉ ። በለፈው ፥
እንደ ፥ አንበብነው ፥ በአንዳንድ ፥ ነገድ ፥ ዘንድ ፥ ሚስት ፤ ልጅ ፥ እናት ፤
ከብት ፥ ሁሉ ፥ የጋራ ፥ ነው ፥ ኤንጂ ፥ እገሊት ፥ የእገሌ ፥ ሚስት ፥ ናት ፥ ብሎ ፥
መወሰን ፥ አልነበረም ። ይኸም ፥ ለዛሬ ፥ ጊዜ ፥ አሰቃቂ ፥ ሲመስለን ፥ በዚያን ፥
ጊዜ ፥ የተለመደ ፥ በመሆኑ ፥ ምንም ፥ አይሰጋበትም ፥ ነበር ።

ጳውሎስ ፥ ፡፡እንዴት ፥ ያምናሉ ፥ መምህር ፥ የሌላቸው ፥ ሐዋርያ ፥ ያልተ
ላከላቸው ፥,, እንዳለው ፥ በዚህ ፥ ዘመን ፥ እንኳን ፥ ሌላው ፥ ሕዝብ ፥ የእሥራኤል ፥
ወገኖች ፥ እንኳን ፥ ሙሴ ፥ በደብረ ፥ ሲና ፥ አሠርቱ ፥ ትእዛዛትን ፥ ተቀ
በሎ ፥ ሕጉን ፥ በእስራኤሎች ፥ ዘንድ ፥ እስኪያጠናው ፥ ድረስ ፥ ይኸ ፥ ልማድ ፥
ሳይደርስባቸው ፥ አልቀረም ፥ አባታቸው ፥ አብርሃም ፥ ሚስቱ ፥ ሣራ ፥ ያባቱ ፥
ልጅ ፥ ኦህቱ ፥ ነበረች ፤ ወንድሙ ፥ ሎጥ ፥ በሸመገለ ፥ ጊዜ ፥ ከሴት ፥ ልጆቹ ፥
ጋር ፥ ይተኛ ፥ እንደነበረ ፥ መጽሐፍ ፥ ቅዱስ ፥ ይናገራል ። ከዚያ ፥ ወዲህም ፥
እስከ ፥ ቅርብ ፥ ጊዜ ፥ ድረስ ፥ ዘራችንን ፥ ከሌላ ፥ አንደበልቅም ፥ በማ